የቅድስት ማርያም እገተ ዕፍረት ገዳል በግዕዝና በአማርኛ



የቄሳ ዘይት ጌቴሴማኒ ቅድስት ማርያም እገተ ዕፍረት
ቤተክርስቲያን ታሪክ

አዘጋጅ እና አሳታሚ የቦታዋ ተወላጅ መ/ር ተስፋሚካኤል ፈለቀ
የትርጓሜ መጽሐፍትና የቅኔ መምህር

Scanned with CamScanner

ገድለ ቅድስት ማርያም እንተ ዕፍረት

በመምህር ተስፋ ሚካኤል ፈለቀ

በግዕዝና እና በአማርኛ

የታሪካማዋና የመስቀልኛዋ ቦታ የቆላ ዘይት ጉቴሴማኒ ማርያም እንተ ዕፍረት ቤተክርስቲያን ታሪክ

አዘጋጂና አሳታሚ፡- መምህር ተስፋ ሚካኤል ፈለቀ

የትርጓሜ መጻሕፍትና የቅኔ መምህር

Scanned with CamScanner

መጀመሪያ በ2002ዓ.ም ታተመ

ይህን መጽሐፍ ደግሞ ለማሳተም መብቱ የአዘጋጂው
ስለሆነ በቀጥታ ገልብጦ ለማሳተም አይፈቀድም

አዘጋጂና አሳታሚ መምህር ተስፋ ሚካኤል ፈለቀ
የትርጓሜ መጻህፍትና የቅኔ መምህር

አድራሻ ኢትዮጵያ አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ቆቦ
ከተማ ደጋጎ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም
0913 57 90 00፣ 0333340793

አዲስ አበባ መስከረም 20 ቀን 2002ዓ.ም

Scanned with CamScanner

ምስጋና

1ኛ ሁሉ በእርሱ ለሆነ ለልዑል እግዚአብሔር እና ለእናቱ ለንጽሕተ ንጹሐን ለድንግል ማርያም

2ኛ በጸሎት፣ በማበረታታትና በገንዘብ ለረዱኝ ለቆሞስ መልአከ ሣህል አባኪዳነ ማርያም ቢሰጥ የቆጥ አንባ ደብረ ምስአል ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ

3ኛ በገንዘብ ለረዱኝ ወንድሞቼ ለአቶ ወንድየ ፈለቀ እና ለአቶ ሲሳይ ፈለቀ

4ኛ በገንዘብ ለረዳችኝ ለክብርት አክስቴ ወ/ሮ በላይነሽ ታየ

5ኛ በገንዘብ ለረዳችኝ ለመንፈሳዊት እሕቴ ወ/ሪት ሽሽግ ነጋሽ የቆበ ወረዳ ልማት ጣቢያ ሠራተኛ

6ኛ በገንዘብ ለረዳችኝ እሕቴ ወ/ሮ የሺ ብርሃኔ የድሬዳዋ ኗሪ

7ኛ ይህን መጽሐፍ በጠቅላላ በኮምፒዩተር በጥራት ለቅማ እና የላይም የውስጥም ሽፋን ዲዛይን አዘጋጅታ ለሰጠችኝ ለወ/ሮ ኑኑ አበሻ

ይህን መጽሐፍ ግዕዙን ከብራና ወደ ወረቀት ገልብጠው እንዳላትመው ፈቃደኛ ሆነ ለሰጡኝ መምህር አባ ሀብተማርያም ተ/ሀይማኖት የቆላ ዘይት ጌቴሴማኒ ማር እንተዕፍረት ደብር አስተዳዳሪ

Scanned with CamScanner

ተ.ቁ	ማውጫ		ገጽ
፩	መግቢያ		፩
፪	መቅድም		፬
፫	በእንተ ብእሲት ኀጥእት ገድል ዘሰኑይ ምፅ		፯
፬	ወእምዝ አሐተ ዕለተ" ዘሠሉስ	፪	፲፱
፭	ወእመዝ ፀንዐት በአሚን	" "	፳፫
፮	ወእምዝ ፀንዐት ማርያም እንተዕፍረት	" ዘረቡዕ	፳፭
፯	ወእምዝ ተንሥአ ፍጡነ	" "	፳፱
፰	ወእምዝ ተዘከረት ልማደ አንስት	" "	፴፫
፱	ወበእንተዝ አለብዎሙ	" "	፴፯
፲	ብፁዕ ውእቱ ዘነቅሀ	" ዘሐሙስ	፴፱
፲፩	ወካዕበ መጽአ	" ዘዐርብ	፵፯
፲፪	ወካዕበ ሖረ	" "	፵፱
፲፫	ወካዕበኒ ይቤ	" ዘቀዳሚት	፶፩
፲፬	ወንህነኒ ናክብር	" ዘእሁድ	፶፭
፲፭	ስምዑ አኀውየ	ተአምር	፶፯
፲፮	ስምዑ አበውየ ወአኀውየ	"	፶፯
፲፯	መልከዐ ማርያም እንተ ዕፍረት	መልከዕ	፷፩
፲፰	የቆላ ዘይት ጌቴሰማኒ ማርያም እንተ ዕፍረት ታሪክ		፷፩
፲፱	የፀደቀው ቤተሰብ ስም ዝርዝር		፷፭
፳	በማርያም ስም የሚጠሩ ሴቶች		፷፱
፳፩	የዐሥሩ መዓርጋት ዝርዝር		፷፱

Scanned with CamScanner

፩ኛ በዘህች መጽሐፍ ውስጥ በግዕዝ ብቻ የነበረው የማርያም እንቁ ዕፈረት ገድል ለግዕዝ ለዋቂዎች ብቻ እንጂ ለመላው ሕዝብ ክርስቲያን ግልጽ አለመሆኑን በመረዳት ለመላው ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ግልጽ እንዲሆንና እንዲያርስ ሲባል በግዕዝና በአማርኛ ለመግለጽ።

፪ኛ አሁን ያለችበት ቤተክርስቲያን በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት በ500ዓ.ም የተተከለች ስትሆን ቦታዋ እንደግሸን ደብረ ከርቤ መስቀለኛ ሆና ዙሪያዋ በነጭ ገደል የታጠረች፣ መግቢያዋ አንድ በር ሲሆን በጠስጣ ይህን ያህላል ተብሎ በቁጥር የማይጠሰን የጥድና የአስታ ዛፍ የሸፈናት በዙሞች ቅዱሳን የሚጸልዩባት፣ ብዙ ተአምራት የሚደረግባት፣ እንደሌሎች ቅድሳን ቦታዎች መጎብኘት የሚገባት፣ ታሪካዊትና ጥንታዊት ቦታ ስትሆን 1501 ዓመት በጭቃ ተገንበታ የሣር እድሳት እየተደረገላት ከአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ወጭ ማንም ሳያወቃት ተደብቃ ስትኖር ሁሉም የኢትዮጵያ ክርስቲያን ይጠቃት ሲባል በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ከተደረገት ታሪክ ለምስክርነት ያህል በከፊል ተጽፎ ይገኛል።

እኔም ይህችን መጽሐፍ ለማዘጋጀት የቻልሁበት ሚስጢር የቅድስት ማርየም እንቁ ዕፈረትን ታሪክ ለይቶ ባለማወቅ ብዙዎች አባቶችና ወንድሞች እንዴ ማርያም መግደላዊት እንዴ የፊያታይዘየማን እሕት የበላዔሰብ ወገን ማርያም

Scanned with CamScanner

ነጥእት ሌላጠ ደግሞ ማርያም ግብጻዊት እያለ ቅኔ ሲቀኙና በመድረክ ላይ ሲያስተምሩ ታሪክ ሲነባ ሰምቼ ማርያም እንተ ሰፍረት የአልአዛር እና የማርታ እሕት መሆኗን ለመግለጥ ነው።

ይኸ ብዙሙኝ አባቶች፣ ወንድሞች፣ እናቶችና እሳቶች የማርያም እንተሳፍረትን ገድል በአማርኛ ተርጉመህ ከቦታዋ ታሪክ ጋር አዘጋጅና ታትሞ ለኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ተሰራጭቶ ታሪካቸን ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን ይወቀው በማለት ጠቁማችሁኝ ስለነበር ነው።

እኔ ልጃችሁና ወንድማችሁ በዘህችው እግዚአብሔር በመስቀል አምሳል በፈጠራት፣ በታሪካማዋ ቦታ ተወልጄ በፓ ቀን ሀብተ ጥልድና ስመክርስት፣ ተጠብዩ ተስፋ ሚካኤል ተበዩ የተሠየምሁበት፣ ፊደል ቆጥሬ ዳዊት የደገምሁበት፣ የቅኔና የመጽሐፍ መምህር ለመሆን ያበቃችን (ያደረሰችኝ)፣ በፓ ዓመተ አፋፍ ብት ወልዳ በ ፲ አመቱ የተለየችን የእናቱ ዕዕም ያረፈባት፣ በተሰቦቱ የሚገለገሉበት ቦታ ስትሆን የመጽሐፍ መ/ር የሆንሁ እንደ ሆነ ገድልሽን ተርጉሜ ታሪክሽን አበጠቡ ለኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን አሳውቃለሁ ብዩ ብዕዓት ገብቼ ጠያ ላለበላ ሬዴሁ። ታቦተ ተ ብዕዓት አድረሽነት፣ የአስብሁት ተፈጽሞልኝ ተመልሼ ዛሬ ነገ ስል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስና የቅዱስ ላለበላ ልደት በዓል ዋዜማ በገቦ ላይ።

Scanned with CamScanner

እንዳለሁ በመከና ግጭት ምክኒያት ወድቁ ሆስፒታል ገብቼ ስታከም ጠይምት ሴት ደመ·ን ከፊ·ቱ እያበሰች አይዞህ የድንግል ማርያም ተረደኢነት የልጇ ቸርነት የእሌም ምልጃ አድኖሃል አንተ ግን የገበሃው·ን ብዐዓት ረሰተሃል አለችኝ። ቀና ብዬ ሳይ የሕክምና ባለ መ·ያዎች ከብበው ግንባሬን ዐይኔን ለይኛው ከንፈራንና ታችኛው ከንፈራን በአጠቀላይ ከአራት ቦታ ላይ ሰፍተው·ኝ አገኘሁ። ስወድቅ ስላልታወቀኝ ወድቄ ነበር·ን? ብዬ ተመልሼ ተኛሁ። ከዚህ በኋላ ቁስሉ ከስድስ ነበር የወልድያ ሆስፒታል ወደ ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ሪፈር ጽፎልኝ ሕክማና ጨርሼ ከሆስፒታሉ ወጥቼ ከተኛሁበት ቤት አንድ አባት ሊጠይቁኝ መጥተው ሰንጨዋወት ያየሁት·ን ራዕይ ነገርኳቸው ጠይሟ ሴት ማርያም እንተዕፍረት ናት። ምን ብለህ ብዕዓት ገብተህ ነበር አሉኝ። ከዚህ በኋላ የገባሁት·ን ብዕዓት አሰታወሼ ከተኛሁበት ቤት በምት·ኛ ላይ እያለሁ በእግዚአብሔር ቸርነት በድንግል ማርያም አማላጅነት በቅድስት ማርም እንተ ዕፍረት ጸሎት ይህን ገድል ተርጉሜ አዘጋጅቼ አሳተምሁ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕገበ ክርስቲያን ይች·ን መጽሐፍ አንብባችሁ ታሪኳን ተረድታችሁ ይች·ን መስቀልኛና ታሪካዊት የሆነች ቦታ በእግራችሁ ተረገጣችሁ በዐይናችሁ አይታችሁ የበረከታ ተካፋይ ለመሆን የቅድስት ማርያም እንተዕፍረት አምላክ ይፍቀድላችሁ ለዘለዓለመ በእውነት ያለሐሰት።

Scanned with CamScanner

መቅድም ማለት መጀመሪያ ከሀ-ሰ አስቀድሞ የሚገኝ የመጽሐፍ መግቢያ በር ማለት ነው። በርን ከፍቶ ወደቤት እንዲገባ መቅድምንም ተመልክቶ ወደ መጽሐፉ የገበ እንደሆነ መጽሐፉ የተጻፈው ስለምን እንደሆነ ዓላማውንም ለማወቅ፣ አዘጋጁውንና አሳታሚውን፣ የታተመበትን አገር፣ የሚያስተላልፈውን መልእክት ለማወቅ ያስችላል። ዳግመኛ አድራሻ አመልካች ማለት ነው። የሀገሩ እንግዳ የሰው ባድያ ሆኖ አድራሻ በጠየቀ ጊዜ። እንደዚህ ያለውን ጎዳና ይዘህ ሂድ ቀኛታ ታገኘዋለህ ብለው እንዲያመለክቱት። መቅድም በመጽሐፍ ውስጥ የሚተላለፉትን ኃይለቃሎች ያስረዳልና። ዳግመኛ ትንቢት ማለት ነው። ትንቢት ገና ወደፊት የሚደረገውን ነገር እንዲገልጽ። መቅድምም መጽሐፉ አመ-ልተው አገ-ልተው የሚናገሩትን ቀንጨፍ ቀንሐፍ አድርጎ ይገልጣልና። ዳግመኛ ርካብ ማለት ነው። ርካብን ተረግጠው ወደኩርቻ ሲወጡ እንዲመች መቅድምንም አንብቦ መጽሐፉን ማንበብ ይመቻልና። ገድል ማለት መጋደል ሰማዕትነትን መቀበል ወገደ ለእግዚአብሔር ብሎ ራስን መካድ ማለት ነው። ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት ከአጋንንት፣ ከከሀድያን፣ ከመናፍቃን ከዐላውያን ነገሥታት እና ከዐላውያን መኳንንት ጋር እየተዋጉ እሳቱን ስለቱን ታግሠው እንደ ጎመን እየተቀረደዱ እንደ ሽንኩርት እየተከተፉ እንደ በግ ሁል ግዜ እየታረዱ።

Scanned with CamScanner

ባሕታውያንና መነኮሳት፡ ዕፀበገዳሙን፣ ድምፀ አራዊቱን፣ ርኀቡንና ጽሙን ታግሠው ጤዛ ልሰው ደዋ ጥሰው ከአጋንንት፣ ከፍትወታት እኩያት፡ ከኀጠውዕ ርኩሳት፡ ጋር እየተዋጉ አግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ ጀምሮ ያዘጋጃት፡ ይህን ትመስላለች ይህን ታህላለች የማይሏት፣ ከገቡባት የማይወጡባት ከአገኙዋት፡ የማያጧት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የሚያደርጉት ትግል ገድል ይባላል። መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፣ ሩጫዬን ጨርሼአለሁ፣ ሀይማኖቴን ጠብቄአለሁ፣ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል። ፪ጢሞ፬፡፮።

ተአምር ማለት ምልክት ማለት። ኖሎ። ጌታ በገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና ሠርግ ቤት የመጀመሪያ ምልክት አሳየ /ተአምር አደረገ/። ዮሐ፪፡፩–፲፩።

በአጠቃላይ በመዋዐለ ስብከቱ ድውያንን ሲፈውስ፣ ለምጽን ሲያነጻ፣ አጋንንትን ሲያወጣና ሙታንን ሲያነሣ ምልክት አሳየ ይበላል። እንዲሁም ቅዱሳን መላእክት፣ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ጻድቃን ሰማዕታት ብዙ ምልክት አሳይተዋል። ኦሪት ዘፍ. ፲፱፡፩-፳፯፣ ፪ነገ.፬፡፴፪-፴፮፣ የሐዋ.ሥራ፫፡፩-፰

መልክዕ ማለተ ከሪስ ጠጉር ጀምሮ እስከ እገር ጥፍር ድረስ ያለው የሰው አካል መልክዕ ይባላል። ስለዚህ ቅዱሳን አባቶችና ቅዱሳት እናቶች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ የዚህን ዓለም ኑሮ ንቀው በሥጋቸው መከራ ተቀብለው ከአለፉ በኋላ የሚያማልዱ ስለሆኑ ጽላት

ይቀረጽላቸዋል ድርሰት ይደረስላቸዋል ይህውም ድርሳን፣ ገድል፣ ተአምር፣ ስንክሳርና መልክዕ በመባል ይገለጣል። እነዘህ እንዲነበቡና እንዲጸለይባቸው መጽሐፍ ቅዱስ አገዛዝ ራዕይ ፩፡፱፡፳ቆሮ ፲፪፡፳፯ መገ. ፵፯።

የቅዱሳት አንስት ቁራቸው ከ፳፪ (መቶ ሃያ) በላይ ነው። መቶ ሃያ ቤተሰብ የሚባሉት ፲፪ ሐዋርያት፣ ፸፪ አርድዕትና ሰባቱ ቅዱሳት አንስት ናቸው። ቅዱሳት አንስት የእግዚአብሔር ባለሟሎች ስለሆነ የጌታን ትንሣኤ ከማየታቸውም በላይ እኛን ለማማለድ ዘወትር ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገሩ እናቶች ናቸው ይሉቱንም ማርያም እንተዕፍረት በ፲፱ ወቂት ወርቅ አድናነ ከሚባል ነጋዴ ሸቀጥ ገዝታ ኃጢአተኞችን ወደንሥሐ ልጠራ ነው እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁ ያለ እግዚአብሔር ኃጢአቷን እንደሚያስተሠርይላት አውቃ ወደ እሱ ሄዳ በእንባዋ እግሩን አጥባ በሀብሯ ከአበሰችው በኋላ ሽቱውን ከራሱ ላይ አፍሰሰች። እግዚአብሔርም ኃጢአቷን አስተሥርዮላታል። በእረኛቷ ጊዜም ቤተክርስቲያንሽን ያነፀውን፣ ገዝርሽን የዘከረውን፣ ገድልሽን ያነበበውንና የሰማውን ከእኔ ጋር አኖረዋለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላታል። አውን ጽላት ተቀርጾላት፣ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶላት ገድል ተጽፎላት በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት በግዳን ወረዳ በ017 ተበሉ በሚባለው መስተልኳና ተራራማ በሆነችው በቆላ ዘይት ጌቱ ሲሞነ ተራራ ትገኛለች። የንግሥ በዓላቶቿ መጋቢት 21 ሽቱ የቀባችበት፣ የነብቷ ፰ ያረፈችበት ነው።

ወር በገባ በ፱ በ፱ ቀን ከቅድስት አርሴማ ጋር ትውላለች።

ገድለ ማርም እንተዕፍረት አብዛሀኛው ወንጌል ነው። የቅድስት ማርያም እንተ ዕፍረት በረከት ይደርብን አሜን።

Scanned with CamScanner

አንደኛ ምዕራፍ

፩ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም አምነን እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ የተመረጠች ሰማዕትና ንዕድ ክብርት የምትሆን የማርያም እንተ ዕፍረትን ገድልና ምስክርነት መናገርን እንጀምራለን/እናስቀድምአለን።

የኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጅ ሽቱ ስለቀባችው ጌታ በአመሰገናት ገንዘብ ከቢታንያ የመጣች። ዕረፍቷም የካቲት ፮ ቀን የሚሆን። ልመናዋ በረከቷ ለዘለዓለሙ ከወዳጇ ከተስፋ ሚካኤል ጋር ይሁን። በእውነት ያለሐሰት።

፪ ቅዱስና ብፁዕ የሚሆን ዮሐንስ አፈወርቅ ጌታን ሽቱ ስለቀባችው ስለማርያም እንተ ዕፍረት የደረሰው ድርሳን ይህ ነው።

፫ የዚህችም ሴት ስሟ ማርያም እንተ ዕፍረት ይባላል። ትውልዷም የአልዓዛርና የማርታ እሕት ናት።

፬ ይህም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሥራውን ሁሉ እንስማ እናስተውልም እሱ በዓለም ሁሉ የታወቀ ነውና እንደሚገባ እንቀበል አለ።

፭ ንጉሥ እንደመንግሥቱ ከፍተኛነት ልዩ ልዩ የሚሰጠው ስጦታ /ፀጋ/ አለና።

ሹምም እንደሹመቱ ከፍተኛነት መጠን ልዩ ልዩ የሚሰጠው ስጦታ አለና። ይህ ግን ለዚህ ለንላፊው ዓለም ነው።

፮ እንደዚህ ካልሆነ ግን የንጉሦችን ንጉሥ የገዢዎች ገዢ

Scanned with CamScanner

መደሚሆን ወደ እግዚአበሔር የሚያቀርበንን በጎ ሥራ ልንሠራ ፈጽሞ ይገባናል።

፮ መንፈሳዊት የምትሆን የማርያም እንተ ዕፍረትን በዓል እናክብር።

፯ ንዕድ ክብርት የምትሆን የዚችን የማርያም እንተ ዕፍረትን መታሰቢያዋንም እናድርግ። ጌታ በወንጌል እውነት እላችኋለሁ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ሥፍራ በሚሰበክበት እርሷዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ እንዲሆን ይናገራል ብሎ እንደተናገረ ማቴ፳፮፡፲፫ ማር፲፬፡፱።

፰ አሁንም መድኃኒትና አለኝታ ሊሆኑን ቅዱሳን አበውንና ሰማዕትን እናስባቸው ዘንድ በፈጣሪ አንደበት የተመሰገኑች ቅድስትና ንዕድ ክብርት የምትሆን የዚች የማርያም እንተ ዕፍረትን ስምዋን እናክብር።

፱ ፍፃሜ የሌላት መንግሥትን እንወርስ ዘንድ በፍጹም ደስታ ልንቀበለው ይገባል።

፲ የቅዱሳን አምላክ የሚሆን የጌታቸውን መምጣት እየተጠባበቁ ተዘጋጅተው እንደሚኖሩ ሰዎች ልባሞችም እንሁን።

፲፩ ከንጉሥ ወይም ከገዥ ዘንድ ደብዳቤ /መልእክት/ በመጣ ጊዜ እነሆ ፈጽመው ደብዳቤውን ከፍ ከፍ ያደርጓታል ያከብሩታል።

፲፪ እንደዚህ ከሆነ በነገሥታትና በሥልጣናት ላይ ጌትነት፣ ልዕልና፣ ሥልጣንና ኃይል ያለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ወልድን ትዕዛዛት ሰባት እጅ

Scanned with CamScanner

እጥፍ ድርብ አድርገን ልናከብር ይገባናል።

ወንጌል ቱታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያባሪያ /ያአገልጋይ/ ንዑድ ነው ክቡር ነው ብሏልና ማቴ ፳፬፡፵፮።

፲፬ በበጎ ሥራ ተዘጋጅተን ሀሊናችንንም ብሩህ አድርገን ልባችንን ወደ እግዚአብሔር እናጋጥጥ «ከመሮጥ ማንጋጠጥ እንዲሉ»።

፲፭ እንደጥላ ታይቶ የሚያልፈውን የዚህን ዓለም አዘን አንዘን።

፲፮ የሚያልፈውንና የሚጠፋውን ሽተን ብንደክም የማያልፈውንና የማይለወጠውን ብንተው ልብ እንደሌላቸው እንስሳት እንሆናለን።

፲፯ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ልዩ ጸም በኛ ዘንድ ደርሷልና በፍጹም ደስታ ልንቀበለው ይገባናል።

፲፰ እንደ ጦመኛ ለሰዎች ይታዩ ዘንድ ፊታቸውን አጥቁረው፣ ሰውነታቸውን አጠውልገው እንደማይታዩ እንደ ግብዞች አንሁን። ማቴ ፮፡፮

፲፱ ግብዞች ናቸውና እንደነሱ አንሁን ወደ ክህደት የማይወስድ ሕጋቸውንም አንከተል። በበጎ ሥራ የተዘጋጀን እንሁን እንጂ።

፳ ከእኛ እያንዳንዳችን እንደ አባቶች በፍቅር እንጹም።

፳፩ የመንግሥተ ሰማያት በር ይከፈትልን ዘንድ መብራታችንንም በክብር እናብራ።

፳፪ እግዚአብሔር ለማወዳትና ትእዛዙን ለማፈጽመው ሰዎች ከአዘጋጀው ከመንግሥተ ሰማያት እንዳንጠፋ።

Scanned with CamScanner

፳፫ ወንድሞቼ ዓለም ስለሚያልፍባት·ና ስለሚጠፋባት· ሰለኀለኛይቱ ቀን ጥበብ፣ እውቀት·ና ማስተዋል ያለው ሰው እነሆ ከዚህ ዓም አዘን ይርቃል /ያመልጣል/::

፳፬ ስለዚህ ስለሰው ብሎ· ወደዚህ ዓለም የመጣ የእግዚአብሔርን መንግሥት· እናይ ዘንድ ልባችንን ልናነፃ ሕሊናችንን ብሩህ ልናደርግ ይገባናል:: መስታው·ት· ራሱ ንዑህ ካልሆነ ፊት·ን ፊጽሞ አያሳይምና::

፳፭ እንደዚህ· ሁሉ ከኃጢአት· ገ·ስቱልና ልቦናችንን ልናነፃ ይገባናል::

፳፮ ቸርነት·ን እንሻት· የጌታንም ት·ዕዛዝ መፈጸም ቸል ቸል አንበል::

፳፯ እነሆ ብዙ ኃጢአት· ሠርተናል ሥርየት· አይገበንም እያልን ከእኛ እያንዳንዳችን አናመሀኝ::

፳፰ ወንድሞቼ ሆይ እንደዚህ አታስቡ· ጥላት· ዲያብሎስ ክፉ· ሃሳብ በልቦናችሁ· ውስጥ ዘርቶ ተስፋችሁን እንዲ·ቆርጡ ያደርጋች·ኋልና::

፳፱ ይህን ክፉ· አሳብ ከእና·ተ· አርቃችሁ· ብሩህ በሆነ ሕሊና /አስተሳሰብ/ና በመልካም ሥራ ወደ እግዚአብሔር ተመልሳች·ሁ ንስሓ ግቡ:: እሱ ያድና·ች·ኋል እሱም ይረዳች·ኋል በደቀመዝሙሩ በጴጥሮስ ላይ እንዳደረገ ይቅርታውን ያበዛላች·ኋል::

Scanned with CamScanner

ጎስቋላውን ልጅ ወንበዴውንና ቀራጩን እንደተቀበለው ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደነሱ ያሉትን ኃጢአታቸውና ደዌያቸው ልዩ ልዩ የሆኑትን ለሁሉም ኃጢአታቸውን አስተሠረየላቸው። ስለ ኃጢአታቸው ብዛት ብሎ ሳያስተሠረይ ያስቀረበት ምክንያት የለም።

፴፩ እነሱም ችል ችል ይሉ ዘንድና ቸርነቱን እንዳይሹ አላደረጋቸውም።

፴፪ ለነፍሳቸው መድኃኒትን ይሹ ዘንድ ሰውን አብዝቶ እንደ ወደደው ልታውቁ ጌታችን ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መጣ ተብሎ በቅዱስ ወንጌል የተጻፈውን እናስተውል። አንደ ሰው መጥቶ ከእሱ ጋር ምግብ ይበላዘንድ እግዚአብሔርን ለመነው ይላልና።

፴፫ ይህን ነገር የምትሰማ ሰውዬው ሆይ ኢየሱስ እንጀራ መብላትንና መጠጥ መጠጣትን ወዶ ወደ እሱ የሔደ አይምሰልህ። ይህን ነገር የሚያስብ ይበድላል እሱ ባለቤቱ በወንጌል ኃላፊውን ምግብ ለመብላት አትድከሙ ለማያልፈው ለዘለዓለም ፀንቶ ለሚኖረው ነው እንጂ ብሏልና።

፴፬ ዳግመኛ እንዲህ አለ የሚፈትነው ሠይጣን በፈተነው ጊዜ ሠይጣን ፵ ቀን ና ፵ ሌሊት ከጸመ በኃላ ተራበ። ፈታኝም ቀርቦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ ይሁኑ ብለህ እዘዝ አለው። እሱም መልሶ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ ነው እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ የተጻፈውን አልሰማህምን? አለው። ማቴ. ፬ ቁ. ፩-፬ ዳግመኛ

እንዲህ አለ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ አይጠማም። ዮሐ. ፮፡፴፭ የሠራው ሥራ ሁሉ ሰለሰምች መድኃኒት ነውና።

፴፩ እነሆ የሰው ልጅ ክርስቶስ የጠፋውን ይፈልግ /ይሻ/ ዘንድ አዳምን ያድነው ኃጢአቱንም ያስተሰርይለት ዘንድ እነሆ መጣ።

፴፪ እንደዚሁ ለበሽታዋ ጤንነትን ለኃጢአትዋ ሥርየት ታገን ዘንድ የመጣች ንዕድ ክብርት የምትሆን ይች ማርም እንተ አፍረትን ጌታችን ወደዳት። ስለዚች መልካም ሴት እንደዚህ ተብሎ ተጽፏልና። በጎሥራዋ የበዛ፣ ደም ግባቷ እጅግ ያማረ፣ ፊጽም ብልጽግናዋ የበዛ።

፴፫ ሁል ጊዜ ነጭ ሐር የተልባ እግር የምትለብስ ከሽቱ ሁሉ ይልቅ የሚበልጥና የሚጣፍጥ /የሚያምር/ ሽቱን ትቀባ ነበር። በፍጹም ወርቅ የምታጌጥ በክፉ ሥራው ሁሉ ጸንታ የምትኖር ወሬዋም /ዝናዋም/ በየአገሩና በየአውራጃው ተሰማ።

፴፬ ጠላት ዲያብሎስ የዚህን ዓለም ሥራ አጣፈጠላት።

፴፭ ነገር ግን ስለዚህች ሴትና ስለ ኃጥአን ሁሉ ጌታችን ከጌትነቱ ከፍታ ሳይለወጥ ከልዑል ዙፋኑ ወረደ። በሰዎች መካከልም ከእነሱ እንደአንዱ እየተመላለሰ አስተማረ።

ከጠላታቸው እጅ ያድናቸው ዘንድ ከድንግል በሥጋ ተወልዷልና። ነቢዩ ኢሳይያስ በኃጢአት ጨለማ በሞት ጥላ ሥር ለነበሩት ሰዎች ብርሃን ወጣላቸው ብሎ እንደተናገረ።

፴፮ እንደዚህም ሁሉ ንዑድ ክብርት በምትሆን በዚች ማርያም እንተ ዕፍረት ላይ የእግዚአብሔር የይቅርታ ክብር ወጣ /ተገለጠ/ ከሲኦል ወደ ገነት ከሞት ወደ ሕይወት ነፃ አወጣት ስሟንም በዓለም እንድትነሳ አደረገ።

Scanned with CamScanner

ምዕራፍ ሁለት።

፩ ከዚህ በኋላ ከእለታት አንድ ቀን ንዕድ ክብርት የምትሆን ማርም እንተዕፍረት እንደልማዷ ነጭ ሐር ለብሳ አጊጣ ፊቷን በመስታውት አይታ ሽቱ ተቀባች።

፪ ጉንጮቿ ቀያዮች ዐይኖቿ የተዋቡ ሆነው ደምግባቷ በጣም አማራት። እንደዚህ እየተመለከተች አንድ ሰዓት ያህል ዘገየች።

፫ ከዚህ በኋላ መልካም አሳብ በእሷ ላይ አድሮ እንደዚህ አለች። ይህን ሁሉ ታስወግድ ዘንድ መልኬንም ትለውጥ ዘንድ ሞት ትመጣ የለምን? ይህ መልካም ሽታ ወደ ትልነትና ወደ ግማት ይለወጣል። ይህስ ብርታት /ጽንዓት/ ፍጻሜው ጉስቁልና ድካም አይደለምን?።

፬ ሊቀርቡኝ የሚወዱትስ የሚርቁኝ አይደሉምን?። እንደዚህም ከሆነ ዘለዓለም ከጥፋትና ኩነኔን ከማብዛት በቀር እንግዲህ ምን አገናለሁ።

፭ የዚህን ዓለም ገንዘብ ብገዛ፣ ብነዳ፣ ባረባ፣ ከሥጋ ጉስቁልና፣ ከድካምና ከዓይኖቼ እንባን ከማፍሰስ የሚያድነኝ ይኖርን? ወይስ ከዚህ ሁሉ ነገር ባዳነኝም ጊዜ ከሞት በሚያድነኝ ገንዘብ ይህ ነገር ይቻላል።

፮ ነፍሴ ሆይ ይፈርድበት ዘንድ ሰው እንደሚናገርበት ቃል ሁሉ እልሃለሁ ያለ ዓለሙን ሁሉ ለሚዝ ጌታ እንግዲህ ምን ትመልሻለሽ።

፯ ነፍሴ ሆይ ከእውነተኛ ፈራጁ ዘንድ በአንቺ ላይ ትዕዛዝ በመጣ ጊዜ እንዴት ትሆኛለሽ። የጨለማ ዳርቻ ወደሚሆን ልትሶ ጥርስ ማፋጨት፣ መዳለበት፣ እሳቱ ወደማይጠፋበት፣ ትሉ

Scanned with CamScanner

፳ ወደማያንቀላፋበትና ውርጩ ወደማይሞቅበት ይወስዱሽ ዘንድ አላቸውና። ነፍሴ ሆይ በዚያ ቀን የሚረዳሽ ማን ነው? ስለአንቺ የሚያማልድሽ ማነው? ንስሐ በሌለበት ነፍስ የተናቀች በምትሆንበት ጩኸትና ልቅሶ በአለበት ቦታ።

፳፩ ነፍሴ ሆይ ከዚህ ከአላፊው ዓለም ታዝን የሚረባሽ የሚጠቅምሽ የለሽም።

፳፪ ይልቁንም ኃጢአት ስለመሥራት ወዳጆቹ አይኖቼ ሆይ የሞት ጥላ በጋረዳችሁ ጊዜ .የሚረባችሁ አለን?።

፳፫ ብዙ የዋጥሁብህ አፌ ሆይ ይህ መብልና መጠጥ የሚረባህ አለን። መራራ የሞት ጽዋን ሳትወድ የግድ በጠጣህ ጊዜ።

፳፬ አንደበቴ ሆይ የዓለሙን ሁሉ ገዥ ትመልስለት ዘንድ የማትችልበት ሞት ዝም ባደገህ ጊዜ እንዴት ትሆናለህ።

፳፭ በእንሶሱላና በቀለበት አጌጣችሁ የምትኖሩ እጆቼ ሆይ የምትፈሩት ሞት በመጣባችሁ ጊዜ እንዴት ትሆናላችሁ።

፳፮ ነጭ ሃርና ጎብሩ ልዩ ልዩ የሆነ ልብስን በመልበስ ደስ የምትሰኝ ሥጋዬ ሆይ በክብር ባለቤት በእግዚአብሔርና ክፉ ሥራህን ይመስክሩ ዘንድ በፊትህ በሚቆሙ ትልፊተ አዕላፍት ረቂቃን በሆኑ መላእክት ፊት ዕራቁትህን በቆምህ ጊዜ እንዴት ትሆናለህ።

፳፯ ነፍሴ ሆይ የዚህ ዓለም መብል የሚረባሽ የሚጠቅምሽ አለን?። በዚያም የትሎች ምግብ ስትሆኝ የሚረባሽ የሚጠቅምሽ አለን?።

፳፰ ሁል ጊዜ ወደ ዝሙት የመትሮጡ እግሮቼ ሆይ ሞት በአሰራችሁ ጊዜ እንዴት ትሆናላችሁ። ልታመልጡም ትወዳላችሁ አይቻላችሁም።

፳፱ ነፍሴ ሆይ በዚህ ዓም የተደሰትሽው ምን ይጠቅምሻል። ንዕድ ክብርት ማርያም እንተዕፍረት ደረታን እየመታች እንደዚህ አሰበች። መድኃኒት ታገኝ ዘንድም የአመለከታትን አታውቅም።

Scanned with CamScanner

፲፰ በሰው ልብ ያለውን መርምሮ የሚያውቅ እግዚአብሔር ግን የጴጥሮስን ልቅሶ አውቆ ንስሐውን እንደተቀበለው ወደ ክብሩም እንደመለሰው የቀራጩንም ጩኸት ከእሱ እንዳላጠፋ። እንደዚሁ ሁሉ ብፅዕት ማርያም እንተዕፍረት በንጹሕ ልብ በመልካም አሳብ ወደእሱ በተመለሰች ጊዜ እንባዋን አልናቀም።

፲፱ እሷ ግን እንዲህ እያለች አሰበች ቸር መምህር እሱ አንደተቀበላቸው እንደ ሌሎች ሰዎች የሚቀበለኝ ነገር ይኖረን? እነግረው ዘንድስ አንድ ሰዓት ያህል ይታገሠኝ ይሆን?፣ ንጉሡ ክፋቴን ሁሉ እንግረው ዘንድ ወደ እሱ የሚያቀርበኝ ይኖር? ጉስቁልናዬንና በደሌን አስታውሰው ዘንድ ይቀበለኝ ይሆን? አንዲት ቃል የሚመልሰልኝ አንዳች ነገር ይኖር? እያለች አሰበች።

፳ ነፍሴ ሆይ ምሕረትስ ቅርብ ናት ባለመድኃኒትም የራቀ አይደለም አንቺ ወደ እሱ ትሄጅ ዘንድ የምትመኪበት፣ መድኃኒትሽን ተስፋ የምታደርጊበትስ አለን?።

ምዕራፍ ሦስት።

፩ ከዚህ በኋላ በማመን ጸጥታ እንዲህ ብላ አሰበች ስለኃጥአን ወደዚህ ዓለም የመጣ ስለነሱ በመካከላቸው እንደሰው የተመላለሰ ይህ አይደለምን? የኃጢአተኛን መመለሱን ነው እንጂ ሞቱን አልሻም ያለስ እሱ አይደለምን?።

፪ መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዲቱ ቢጠፋ፣ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኝ ድረስ ሊፈልጋት የሚሄድ አይደለም? ባገኛትም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከማታል ካልጠፋት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ ፈጽሞ ደስ ይሰኝባታል።

Scanned with CamScanner

፫ እናንት ደካሞች ሸክማችሁ የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም
አሳርፋችኋለሁ የሚል እሱ ነው። ሉቃስ ፲፩፡፳ ማቴ. ፲፩፡ ፳፰
እንደዚህ ከሆነ ለምን እሰንፋለሁ? ለምንስ ንስሐ አልሻም እነሆ
ከዛሬ ጀምሮ ወደ እሱ ሂጄ እራሴን በፊቱ እክዳለሁ። ካልተወኝ
እርሱ ይቅር ባይ፣ መሐሪ፣ ይቅርታውና ቸርነቱ የበዛ እንደሆነ
እነሆ አውቃለሁ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባይቀበልኝም
እበሳጭ ዘንድ ፈጽሞ አይገባኝም።

ምዕራፍ ፬ የሮብ

፬ ከዚህ በኋላ ብፅዕት ማርያም እንተዕፍረት ተጽናንታ በፍጥነት
ተነሥታ የገዛችውን ገንዘብ ወርቁንና ብሩን ሁሉ ሰብስባ።
እንዲህ ብላ አሰበች። እንግዲህ ምን አደርጋለሁ ይህንን ገንዘብ
ወደ እግዚአብሔር ብወስደውም አይቀበልም። እሱ ፈጣሪ፣ ጌታና
የዓለም መድኃኒት ነውና።

፭ ከዚህ በኋላ ሽቱ ወደ ሚሸጥ ሰው ፍለጋ ሄደች ያን ሰው ከጥንት
ጀምሮ ታውቀው ነበርና ከእርሱ ዘንድ ፈጽማ ሽቱን ገዛች።

፮ ያም ሰው በአያት ጊዜ ደንገጠ። ንዕድ ክብርት ማርያም እንተ ዕፍረት
ብሎ ጠርቶ ምን ሆንሽ አለት። በአንቺ ላይስ የመጣው ምንድን ነው?።

፯ ከሚወዱሽ ወዳጆችሽ የሞተ አለን?። ስለዚህ ነገር ስለእሱ ፈጽመሽ
አዘናሻል። ሙታንን ትቀበያቸው ዘንድ ልትገዢ ትወጂአለሽን?። ወይስ
ያየሽው መልከ መልካም አለን በፍቅሩ ታነዳሻልን? ወይስ ፈጽሞ
ገንዘቡ የበዛ ከትልቅ ከተማ የመጣ መልከ መልካም ነጋዴ አይተሽ።
ስለዚህ ነገር በእሱ ላይ ልታመካኚ ትወጃለሽ። ወደዝሙት
ወጥመድስ አስገብተሽ ገንዘቡን ትወስድበት ዘንድ።

Scanned with CamScanner

እንደዚህም ባለ ነገር ብዙ ጊዜ ተናገራት። ከመልካም ሥራዋ የተነሣ ጠላት ዲያቢሎስ /ሠይጣን/ ክፋትን በልቡ ዘርቶበታልና።
ንዕድ ክብርት የምትሆን ምርጥ እቃ ማርያም እንተዕፍረትም መለስችለት ሰውዬ ሆይ ከዐይኖችህ አንዱ ምንድን ነው ከወዳጆችሽ የሞተ አለን ላልኸኝ አምን ብዙ ጎጢአቴ ሙቶ ልቀብረው እወዳለሁ። መልከመልካም ጕልማሳ አይተሽ ላልኸኝ ዳዊት ከሰው ልጆች ተለይቶ መልኩ ያማረ ብሎ እንደተናገረ እነሆ የሰዎችን ሰውነት የሚያድን መጣ እነሆም የማያልቅ ክብርን የሚሰጥ ይሆን ዘንድ ወደድሁ። የመንግሥተ ሰማያትን ርስት ይከፍለኝ ዘንድ። በጥቂት ገንዘብ ብዙ ገንዘብ የሚሰጥ ነጋዴ ወዳጅ ከከተማ መጥቶብሽ ላልኸኝም አምን መልካም ብለሃል። ነጋዴ በቅናሽ ገዝቶ በውድ ሸጦ እንዳተርፍ ረብሕ ጥቅም እንዲያገኝ እሱም የሚጠፋውንና የሚለወጠውን ወስዶ የማያረጀውንና የማይጠፋውን ይሰጠናልና። በምድር ስለአለው ፈንታ በሰማያት ያለውን ይሰጠኛል።
አሁንም ወደሱ እሄድ ዘንድ እወዳለሁ ፍለጋውንም እከተለው ዘንድ ሌላም አይደል። አሁንም የምለው ሌላ አይደለም በአመፅ የሰበሰብሁት ገንዘቤን ከእኔ ወስደህ እጅ መንሻ አድርግ እለዋለሁ።
ሽቱ የሚሸጠውም ነገሯን በሰማ ጊዜ ደነገጠ። ያመጣችለት ገንዘቧ ብዙ እንደሆነ አይቷልና። በልቡ እንዲህ አለ የወደደችውን ባልሰጣት እነሆ ወደሌላ ሂዳ በእሱ ዘንድ የወደደችውን ትገዛለት እኔም ይህን ያህል ገንዘብ አበላሻለሁ። ዋጋው ብዙ የሆነና ሽታው የሚጣፍጥ ሽቱ በእሱ ዘንድ ነበርና።

Scanned with CamScanner

ምዕራፍ ፫።

፩ ከዚህም በኋላ ፈጥኖ ተነሥቶ ያንን ሽቱ አሳያት።

፪ ያችም ሴት ፈዕማ እየተደሰተች ተመልሳ ሄደች።

፫ እየተደሰተች ስትሄድ እነሆ ሠይጣን በጠርቅ ያአጌጠች ሴት መስሎ ወደ እሷ መጣ። የዚህን ዓለም ምኞት እያጣፈጠ ይነግራት ጀመር። መበላትን መጠጣትን ያማረ ልብስ መልበስን ዕጣን ማጤስን ሽቱ መቀባትን ያሳስባት ጀመር።

፬ ልቡናን መርምሮ የሚያውቅ ጌታችን ግን በይቅርታው ብዛት የጠላት ዲያብሎስን ክፋት ገለጣለት። ሠይጣን ከእኔ ወግድ ብላ በቁርጥ ነገር መለሰችለት። ለበደልና ለኃጢአት ሥራ የተዘጋጀሁ አድርገሽኛልና። ኃፍረትና ገስቁልናን በእኔ አመጣህ።

፭ አሁንም ሁሉን ወደሚገዛ ጌታ እሄዳለሁ። የሚከተሉትንና የአመኑትን እሱ አዘዛቸው ወርቅ ብር ወይም ናስ በመቀነታቸው ለመንገድም ከረጢት እንዳይዙ። ነገር ግን ወደሚገባው እኔዳለሁ።

፮ ንዕድ ክብርት የምትሆን ማርያም እንተዕፍረትን ጌታ አቀረባት።

፯ የሃይማኖትዋን ጽናት ጥላት ዲያቢሎስ በአየ ጊዜ ከእሷ ሸሽቶ ፈሪሳዊ ወደሚሆን ሰው ሄደ። ስምዖንም ጌታ ኢየሱስን ወደምሣ ጠራው በዚያም የስምዖንን ልቡና ያውክ ጀመር እንደዚህም እንዲል አደረገው ይህስ ነቢይ ቢሆን ይች የምትዳሰሰው ሴት ማን እንደሆነች እንዴትስ እንደነበረች ኃጢያተኛ እንደነበረች ባላወቀም ነበር? እንዲል አደረገው። ሉቃ፡ ፯፡ ፴፱

፰ ከመድኃኒታችን አኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ወልድ አንድነት ሊለጠፋት ጠላት ዲያብሎስ ይህን አደረገ።

Scanned with CamScanner

፱ ይችውም ማርያም እንተ ዕፍረት በማመን ጸንታ ወደእሱ ሄደች።
ደጆች ተከፍተው አገኘች ያለማፈር ገብታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ደረሰች።

፲ በዓይኖቻቸው የአይዋትም ሁሉ ይችን ሴት አደነቋት።

፲፩ እሷ ግን በስተኋላው በእግሩ ኣጠገብ ቆማ እያለቀሰች በእንባዋ ታርስ ጀመረች፣ በራስ ጠጉርዋም ታብሰው እግሩንም ትሰመው ሽቱም ትቀባው ነበረች።

፲፪ ማርያም እንተ ዕፍረት እንዲህ አለች ነፍስንና ሥጋን የምታድን የእግዚአብሔር አካላዊ ቃል ሆይ፣ የሕይወት ምንጭ ሆይ ሕይወቷን ወደአሳመርህላት ወደ አገልጋይህ ተመልከት። እኔ ግን አንተን በድያለሁ ዳግመኛ ክብርን ብፅልን ሰጠኸኝ። እኔ ወነጀልሁ እንደ እንሰሳ ሆንሁ እንደነሱም የተቆጠርሁ ሆንሁ ኃጢአተኛና ችግረኛ የምሆን እኔን አቤቱ ይቅር በለኝ ማረኝ። ከኃጢአት ቀመበር በታች ሆኜ ለሠይጣን ተገዝቻለሁና ጌታዬ ከሠይጣን እጅ አድነኝ ቀላል የንስሓ ቀንበርን እሸከም ዘንድ የበቃሁ አድርገኝ የምሀረትህንም በር ክፈትልኝ ይቅርታህንና ሥርየትህን ተስፋ አድርጌ ወደ አንተ የመጣሁ አገልጋይህን ጌታዬ ተቀበለኝ።

፲፫ ዳግመኛ ነፍሴ ሆይ መድኃኒትሽን እንዴት አትሽም። እነሆ መድኃኒት ክርስቶስ በዚህ አለና ለምንስ ለደቄሽ ፈውስን አትፈልጊም ባለመድኃኒት ሳለ። ከቆሻሻነትሽስ ለምን አትጸጅም በፈትሽ የሚፈስ የሕይወት ውሃ ምንጭ እያለ።

፲፬ እንደገና እንደዚህ አለች ከንቱ ነገርን ስትመለከቱ የኖራችሁ ዐይኖቼ ሆይ ጌታን ታዩ ዘንድ ተሠጣችሁ ርኩስን የምትዳስሱ እጆቼ ሆይ የሰማያዊ የጌታን እግር ትዳስሱ ዘንድ ተሠጣችሁ።

Scanned with CamScanner

፲፩ ከመለኮቱ ማቃጠል የተነሣ አትፈሪምን? ከበሽታሽ ሁሉ ይፈውስሻልና ከርኩሰትሽ ሁሉ ያነጻሻልና።

፲፪ ኀጢአተኛ ነፈሴ ሆይ እነሆ ፈጽሞ ከፍ ያለ ባለሟልነትን አገኘሽ። ስለአደረገልኝ ምን እከፍለዋለሁ ብሉ ነቢይ ዳዊት እንዳመሰገነ ልታመሰኝ ይገባሻል ንዕድ ክብርት ማርያም እንተ ዕፍረት ታላቅ ልቅሶ እያለቀሰች እንደዚህ ተናገረች።

ምዕራፍ ሰባት።

፩ ከዚህ በኋላ የሴቶችን ድካም አስባ ጨከነች የጌታንም እግር ይዛ በእንባዋ እያራሰች በአራሷ ጠጉር ታብስ ጀመረች። አስቀድማ በልቧ እንዲህ ብላ አስባለችና። በጌታ ፊት ባለማልነትንስ ከአገኘሁ ወደእሱ ዘንድ እንድቀርብ ያደርገኛል።

፪ በሥራዬ ክፋት ከአበረረኝ ግን ዳግመኛ አልድንም።

፫ አቤቱ በቸርነትህና በይቅርታህ ብዛት በዚያ ከሚኖሩት ይልቅ የተናቀች አገልጋይሽን ወደአንተ አቅርባት፡ ከእሱ ባለሟልነትን ባገኘች ጊዜ ጨክና በራሱ ላይ ሽቱ ጨመረች።

፬ ከዚህ ሁሉ ጋርም ልቅሶና ወደእሱ መለመንን አላቋረጠችም።

፭ የእግዚአብሔር ስጦታ በእሷ እንደበዛ ባየ ጊዜ ጠላት ዲያቢሎስ በእሷ ላይ ታላቅ መቅናትን ቀናባት።

ተቆጥቶም ወደ ስምዖን ተመልሶ ልቡን አወከው እንዲህ እያለ እንዲያስብ አደረገው። ይህስ ነቢይ ቢሆን ይች ይምትዳሰሰው ማርያም እንተ ዕፍረት ኀጢአተኛ እንደሆነች ባላወቀም ነበርን እንዲል አደረገው።

Scanned with CamScanner

፮ ስለዚህ ነገር ጌታችን ስምዖንን አሳቡ ከእሱ እንዳልተደበቀ ልብ ያስደርገው ዘንድ ወደደ። ስለእሷ ያሰበውንም ልብ አስደረገው፡ ማቃለልንም ከእሱ ያርቅ ዘንድ። በጎጠአተኛውም እንዳይመካ።

፯ ዳግመኛ እግዚአብሔር በደለኞችን ማዳን እንደሚችል ከጎጠአታቸው ማንጻት እንደሚችል ያውቅ ዘንድ እንዲያስተውል አደረገው።

፰ ስለዚህ ነገር ስምዖንን የማስፈረድ ነገር አለኝ አለው።

፱ መምህር ሆይ በል ተናገር አለው።

፲ ጌታ ኢየሱስ ክርክቶስም ለአንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት በአንዱ አምስት መቶ ዲናር ነበረበት በሁለተኛውም ሃምሳ ነበረበት። የሚከፍሉትም ቢያጡ ለሁለቱም ተወላቸው። እንግዲህ ከእነሱ አብልጦ የሚወደው ማንኛው ነው አለው።

፲፩ ስምዖንም መልሶ ፍረድስ ካልኸኝ ብዙ የተወለት ይመስለኛል አለ።

፲፪ እሱም በእውነት ፈርደሃል አለው። የተመረጠችና ንዕ ክብርት ወደመትሆን ወደ ማርያም እንተ ዕፍረት መለስ ብሎ ስምዖንን እንዲህ አለው። ይችን ማርያም እንተ ዕፍረትን ታያት አለህን? እኔ ወደቤትህ ገባሁ ውኃ ስንኳ ለእግሬ አላቀረብህልኝም። እርስዋ ግን በእንባዋ እግሬን አራሰች የሐር ጉንጉን በሚመስል ጠጉርዋም አበሰች። አንተ አልሳምኸኝም። እስዋ ግን ከገባች ጀምሮ እግሬን በከንፈሮቿ ከመሳም አላቋረጠችም። አንተ እራሴን ዘይት አልቀባኸኝም እርስዋ ግን እግሬን ሽቱ ቀባች። ስለዚህ እልሃለሁ እጅግ ወደኝአለችና ብዙ ያለው ጎጢአቷ ተሠርዮላታል ጥቂት ግን የሚሠረይለት ጥቂት ይወደኛል።

Scanned with CamScanner

፲፫ እርስዋንም ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል አላት።

፲፬ ከእርሱ ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩት ርስበርሳቸው ኀጢአትን እንኪን የሚያስተሠርይ ይህ ማን ነው ይሉ ጀምር።

፲፭ ንዕድ ክብርት ማርያም እንተ ዕፍረትን እንዲህ አላት እምነትሽ አድኖሻልና በሰላም ሂጂ አላት ሉቃ፯፡፶-፱ እኔ ላደርገው የምወደውን ሥራ አይከለክሉኝም ስለኃጥአን ብዬ ወደዚህ ዓለም መጥቼአለሁና ስለጠላት ዲያብሎስ ብዬ ምሕረቴን ወደ እኔ ከሚመለሱ ሰዎች የማርቅ አይደለሁም። እነሱ የሰውን ፊት ያያሉና እኔ ግን ልብንና ኩላሊትን እመረምራለሁ። ፈጽሞ ደስ ይበልሽ ኃጢአትሽን አስተሥርዮልሻልና። ስም አጠራርሽንም ለዘለዓለም ያስቡ ዘንድ አድርጎልሻልና።

፲፮ እነሱ በእርስዋ ይህን ያህል ሽቱ ስለምን አበላሸች እያሉ እነሱ በእርስዋ እንጎራጉረዋልና። ለነዲያን ምጽዋት ይሰጡት ዘንድ ለሦስት መቶ ወቄት ወርቅ ባልተሸጠም ነበረን? እያሉ።

ምዕራፍ ፯ የሐሙስ

፩ ስለዚህ ነገር ብፁዕት ማርያም እንተ ዕፍረት ያደረገችው ይሻላል እንዲሉ እግዚአብሔር አደረጋቸው። ስለእርስዋ እንዲህ እያለ ምጽዋትስ የቀና ሃይማኖት በሌላቸውና ልቦናቸው ብሩህ ባልሆነ ሰዎች ዘንድ የተናቀች ትሆናለች።

፪ እናንተ ግን በዚች ሴት የምትቀኑባት ጠላት ዲያብሎስ በልቡናችሁ ከፉ ዘርን ስለዘራባችሁ ነው።

፫ ለድሆች ትራሩላቸውን ዘንድ ለድሆች ብታስቡ ግን ወደ እኔ በሚመለሱ ሰዎች ፊት የምሕረት በርን እንዴት ትዘጋላችሁ። ምጽዋት ሰውን ወደ እግዚአብሔር ታቀርበውአለችና።

Scanned with CamScanner

፩ እነሆም ይች ምርጥ እታ ማርያም እንተ ዕፍረት ገንዘብዋን ሁሉ አመጣች ያስቀረችው ምንም የለም። መልካሙ ነገር ሁሉ እንደተፈጸመላት አውቃ።

፪ ስለዚህም ነገር ድንቅ ስጦታ (ጸጋ) ተሰጣት። እግዚአብሔር አእኛ ያለ ንስሐ በክንቱ እንጠፋ ዘንድ አይሻምና በንጹሕ ልብ ወደ እሱ እንቀርብ ዘንድ ከኃጢአታችንም እንመለስ ዘንድ ነው እንጂ።

ምዕራፍ ፫።

፫ ከስንፍና እንቅልፍ ነቅቶ ስንፍናን ከእሱ ያራቀ ሰውን ነውድ ነው ክቡር ነው። በጎ ሥራን ያሰበ፣ በር ሳይዘጋ መግበት የሚፈልግ፣ ጠያው ሳይታጎል (ሳይፈታ) ለመብራት ዘይት የገዛ ሰው ንውድ ነው ክቡር ነው። እግዚአብሔር የንስሐ መንገድ ሰጥቶናልና።

፬ ይልቅም ስለነፍስና ስለሥጋ መድኃኒት ፈንታ ክፉትን ሁሉ ታርቅ ዘንድ ንስሐ ስለገባች ንዕድ ክብርት ስለምትሆን ስለማርያም እንተ ዕፍረት በጎ ሥራዋ ያሰበ ብፁዕ ነው። እነሆ የስንፍና ዘመን አልፏልና።

፭ መጥመቀ መለኮት ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ያስተማረው የንስሐ ጊዜ እነሆ ደረሰ።

፮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም መጣ ከኃጢአት ቀንበር መገላት ያድነን ዘንድ። አዳኝ በሆነ በመስቀሉ ኃይልም ያድነን ዘንድ። የቀናች ሃይማኖትን ሰጥቶ ልዩ በሆነች ትንሣኤው ከወደቅንበት ያነሣን ዘንድ። የዘላለም እድል መንግሥተ ሰማያትንም ያደለን ዘንድ።

፯ እንደሚገባ ጸጋውን እንቀበል ዘንድ ዕዳችንንም እንከፍል ዘንድ ይገባናል።

Scanned with CamScanner

ማጠቃለያ በሐሙስ ቀን የሚነበብ የማርያም እንተ ዕፍረት ገድል

፮ የንስሐ ጾምን እንጹም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ስንፍናና ያለ ቸልታ ስለእኛ አርባ ቀንና አርባ በሌሊት ጾመልናልና።

፯ ከክፉ ሥራ ሁሉ እየራቅን መልካም እንሠራ ዘንድ ያለ ነቀፋ የንስሐ ጾም ልንጾም ይገባናል። የሚያጠግብ ምግብ ከመብላት የሚያሰክር መጠጥ ከመጠጣት ጾም ይሻለናልና።

፰ ነገር ግን ጾም ብቻ የሚረባ የሚጠቅም አይደለም በደላችንንና ኃጢአታችንን እያመንን ከቸርነት፣ ከምጽዋትና በብሩህ ገጽና በንፁህ ሀሳብ ሆነን ከፍቅር ጋር መታመን ነው እንጂ ።

፱ የበደሉንን በደላቸውን ይቅር እንበል እንባም አውርደን የኃጢአታችንን እድፍ እንጠብ። ምርጥ እቃ የተባለች ይህች ማርያም እንተ ዕፍረትንም በንስሐ እንምሰላት ለደቄያችን መድኃኒት ለኃጢአታችን ሥርየት እናገኛለን። ጌታችንና መድኃኒታችን እውነት እውነት እላችኋለሁ

Scanned with CamScanner



Scanned with CamScanner

እንኳን አደረሳችሁ!

የቀፀባ ማርያም አጭር ታሪክ

ከ12ኛው መቶ ክ/ዘመን በፊት እንደተመሠረተች የሚነገርላት ይህች ቤ/ክ የምትገኘው በሰላሌ አውራጃ ደብረ ሊባኖስ አካባቢ ከፍኖተፅድቅ ዝቅ ብሎ ነው:: ይህችም የድንጋይ አጥሯ በመባል ትታወቃለች:: ከድንጋዮችም መካከል ባለ ሦስት ጉልላት ሥውር የሥላሴ ቤ/ክ ይገኛል የግራኝ ኣመቤት ትባላለች:: ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያኗን ሊያፈርሳት ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ ሊጥል ሲል እመቤታችን በቀኝ በኩል በምትመለከቱት ዋሻ ስር እንደተሠወረችበት ይነገራል:: ያም ድንጋይ /ቋጥኝ/ ከገደል ጫፍ እስከ አሁን በአየር ላይ ተንጠልጥሎ ለታሪክ ይታያል:: ዳግመኛም ታላቅ ቃልኪዳን የተሰጣቸው የጻድቁ የአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ጽላት በዚህ ይገኛል:: በበረከት የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና ኢያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ::

2ኛ ቆሮ ም.9 ቁ.7

ፎቶና ዲዛይን
ገረመው ደመቀ

አሳታሚ
ቀፀባ ማርያም
☎ 0116-56 35 71

ዋጋ 1:00

ሁለትም ሦስትም ሆነው ቢለምኑት ስለሀዘን ቢተባበሩ ከአባቴ ዘንድ ይደርግላቸዋል። ሁለትም ሦስትም ሆነው በስሜ በሚጸልዩበት ቦታ በመሀከላቸው አለሁ ብሏልና።

፲ ስለዚህ በማመን ወደ እሱ የሚመለሱትን ልመና እሱ እንደሚቀበል አለበማቸው። ንስሐ ለገባችና ምርጥ እቃ ለሆነች ለዚች በፅዕት ማርያም እንተዕፍረት እንዳደረገ ባለሟልነትን ለአገኙ ለብዙዎች ሌሎች ሰዎችም እንዳደረገ በቅዱስ ወንጌል ተናግሯልና።

፲፩ እናንተም ጌታችንስ አይተነው ቢሆን ትእዛዙን ማድረግ በአበዛን ነበር እያላችሁ አተመሀኙ። እንደዚህ ያለው አሰብ ከሀይማኖታችሁ ጉደለት የተነሣ ይሆናልና። የመንፈስቅዱስ የለጋስነቱ ሰጠታ ሰውነታቸውን ክርሱስ ነገር ሁሉ አንጽተው እግዚአብሔርን በመፍራት በሚያመልኩ ሰዎች አድሮ ይናገራል።

፲፪ ስለዚህ ነገር እንደምርጥ እቃ እንደ እስጢፋኖስና እንደ ጥበበኛ ቈርኔሌዎስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያዩ ዘንድ የተዘጋጁ /የበቁ/ ሆኑ እግዚአብሔር በግልጽ የታያቸው ሰዎች ልባቸውን ንጹሕ አድርገው ጎሊናቸውን ለዕውቀት ብሩህ አድርገዋልና።

፲፫ ከክፉ ሥራ እንርቅ ዘንድ ይገባናል ነፍሳችንንም ሥጋንችንንም ንፁህ አድርገን መንፈስ ቅዱስ ያድርብን ዘንድ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እናንት የክርስቶስ ማደሪያ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ በላያችሁ እንዳለ አታውቁምን? የእግዚአብሔርን ቤት ያፈረሰ እሱን እግዚአብሔር ያጠፋዋል። ቤቱም የተባላችሁ እናንተ እራሳችሁ ናችሁ ብሎ እንደተናገረ።

፲፬ ስለዚህ ነገር ነፍሳችንን ሥጋችንንም ከርኩስ ነገር ፈጽመን ንፁህ እናድርግ በበጎ ሥራም ጸንተን እንኑር መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ ያድር ዘንድ።

Scanned with CamScanner

፵፮ በሐሙስ ቀን የሚነበብ የማርያም እንተ ዕፍረት ገድል

፲፭ ወደክፉ ሥራ ብንመለስ ግን እነሆ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ይለያል። የአጋንንት ማደሪያዎች እንሆንለን ቅዱስ በቅዱሳን ላይ ነው እንጂ በክፉ ሠሪዎች ላይ አያድርምና።

፲፮ ዳግመኛ እግዚአብሔር በወዳጆቹ ላይ አድሮ ይኖራል አለ።

፲፯ በክፉ ሥራ ጸንተው የሚኖሩና በደልንና ኃጢአትን በማድረግ ሐዋርያ ሆነው የሚኖሩ ግን በቅዱስ ወንጌል ስለነሱ ተናግሯል ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ ዕረፍት እየፈለገ ውሃ በሌለበት ቦታ ያልፋል አያገኝም በዚያን ጊዜም ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል ቢመጣም ባዶውን ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል ከዚያ ወደዚያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎች አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል ገብተውም በዚያ ያድራሉ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኃለኛው ይብስበታል ማቴዎስ ፲፪፡፵-፵፭ እነሆ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሕግ አስተምሮናል ከክፉት ሁሉም እንርቅ ዘንድ አዞናልን።

፲፰ እግዚአብሔር ለእኛም ለእናንተም የጸጋውን ስጦታ ያድለን፣ በመንግሥተ ሰማያት የተዘጋጀን ያድርገን፣ በእሱ ዘንድ ሥርየትንና መድኃኒትን አግኝታ የተመረጠች ከሆነች ከዚች ንዕድ ክብርት ማርያም እንተዕፍረት ጋር አንድ ያድርገን።

፲፱ በዚች ቅድስት ጾመም ኃጢአታችሁን የስተሠርይላችኋል። መንግስተ ሰማያትንም ያወርሳችኋል ዘወትርም ከወዳጆቹ ጋር አንድ ያድርጋችኋል።

፳ ከቅዱሳን አባቶች አንዱ ስለዘህ ሽቱ ምን እንደሆነ ነገረን። ዘይት ነውን ምንድነው ወይስ ቅባት ነውን ወይስ ተመረመሪም ከቀመመሙት ከሽቱውን ነውን አያልን እንደንጠረጠር።

Scanned with CamScanner

፭፩ ይህን ሽቱ የማጠችለት ማርያም እንተዕፍረትን በጣም ወደዳት። ይህች ሽቱ በሥጋዬ ላይ የጨመረች ይህች ሴት ለምቀበርበት ቀን አስጠበቀች እያለ በጣም ወደዳት። እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህ ወንጌል በተሠበከበት በዓለም ሁሉ ዘንድ የተመሰገነች ማርያም ያደረገችውን ያንብቡ ሕገዘቡም አሕዛቡም በክብሯ ቀን ያሰቧት ክፍክፍም ያድራጓት። ለወዳጇ ለማርያም እንተዕፍረት ከአፌ የወጣው የማልሁት አይዋሽም ያስብዋት ዘንድም በራሴ ማልሁ። ለዘለዓለም በእውነት ያለ ሐሰት።

ምዕራፍ ፱ የዐርብ

፩ ዳግመኛም መልካም አሳብ ወደ እኔ መጣና ለመንሁ ወደ እግዚአብሔርም አንጋጠጥሁ ይህ ሹቱ ምን እንደሆነ አውቅ ዘንድ።

፪ እነሆም የእግዚአብሔር ወዳጅ ደግ ሰው እንደዚህ አለኝ እመቤትችን የይሁዳ አውራሽ ወደ ምትሆን ቤተልሔም ስትደርስ የመውለጃዋ ቀን በደረሰ ጊዜ አዋለጪ አመጡላት እመቤታችንም በሐሳብ፣ በአውቀትና በጥበብ ሁሉ ላይ ድንቅ በሚያሰኝ ልደት ልጅ በወለደች ጊዜ አዋላጪቱ ሕፃኑን አንስታ ያዘችው። በሕፃናት ላይ እንደሚደረገው እንደ ዘይት አቀባብ ሥርዓት ዘይት ትቀባው ዘንድ።

፫ ከዚህ በኋላ አዋላጪቱ ዘይት አመጣች እጆቿንም በእዚያ ቅብዓት ላይ አስቀመጠች የሕፃኑን አካል ትቀባው ነበር። እንደሱ ያልሆነ ጣፋጭ ሽታ ይሸታል እነሆም ይወጣ ነበር።

፬ እሷ ግን በእጅዋ ላይ አድርጋ ባሸተተች ጊዜ የሽቱውን ጣፋጭነት /ማማር/ አደነቀች ሕፃኑን ቀብታ በጨረሰች ጊዜ የአዋላጪቱ እናት የዚያን ዘይት ትራፊ ለብዙ ዘመን በቤትዋ ውስጥ ደብቃ ከእስዋ ዘንድ አስቀመጠች የሽቱውም ሽታ ከሽቱ ሁሉ ይበልጣል ከናትራ የሽቱውም ጣፋጭነት ከሚሸጠው ሽቱ ሁሉ ይበልጣል።

Scanned with CamScanner

፫ ከዚያች አገር ገዥ ዘንድ እንዳያካስሷት እና እንዳያጣሏት ፈራች።

፮ ስለዚህ ነገር ምን እንደሆነ ሳያውቅ በብዙ ገንዘብ ሽቱ ከሚገዙ ነጋዴዎች ለአንዱ አውጥታ ሸጠችለት አሷም ያ ሽቱ ምን እንደሆነ የነገረችው ምንም ምን የለም።

ምዕራፍ ፲።

፩ ዳግመኛ በበጎ ሥራ የጸና ከቀደመ አባቶች ወገን አንዱ ሔደ። ስለዚህ ሽቱ አጥብቄ ጠየቅሁት።

፪ እንደዚህ አለ ርጉም በሆነ በሔሮድስ ዘመን ዮሴፍ ሕፃኑንና የሕፃኑን እናት እመቤታችንን ይዞ በሸሸ ጊዜ ወደ ምድረ ግብፅ ሄዱ በጎዳናም ሲሄዱ በፈረስ ላይ የተቀመጠ እነሆ አንድ ሰው ከእነሱ ዘንድ ነበር። ከእርሱ ጋርም መንገድ ይሄድ ዘንድ ጀመረ። እመቤታችን ድንግል ማርያም መንገድን በመሔድ እንደደከመች ባየ ጊዜ ሕፃኑን አንሥቶ በጭኑ ታቀፈው። በፈረስ ላይ ሳለም የመልካም ሽቱ ሽታ ይሸት ነበር።

፫ የሕፃኑ ወዝ ሲንጠፈጠፍ ባየ ጊዜ መልካም ሽታም እንዳለው ይልቁንም መልካም እንዲሸት ባየ ጊዜ ያ ሰው ሻሹን ከራሱ አውልቆ የሕፃኑን ወዝ ይፈልግ ጀመር።

፬ ከዚህ በኋላ ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስን ሰጥቷት በሌላ ጎዳና ሔደ። ወደ ቤቱም በደረሰ ጊዜ ታጥበው ዘንድ ልብሱን ለእናቱ ሰጣት።

፭ እሷም እንደሱ ያልሆነ ጣፋጭ ሽታ ከሻሹ ውስጥ አሸተተች በማጠቢያውም በአስቀመጠችው ጊዜ ከሻሹ ውስጥ ሽታው የሚጣፍጥ ዘይት ወጣ ሽታውም እጅግ ይጣፍጣል። እሷም ከቅባቷ ጋር በማሰሮ ዘግበ አስቀመጠችው እጅግም ይጣፍጣል ነበር።

Scanned with CamScanner

በሁላችው ቅዱሳንና ሰማዕት ጸሎት ይጠብቃችሁ።

፮ ያ ዘይት ባለባት በዚያች መንገድ የሚይዜዱ ሰዎች የሽቶውን ጥፍጥና ያደንቁ ነበርና ስለዚህ ያች ሴት እንዲያከሷት ፈርታ ብዙ ሽቱ ለሚገዛ ሰው ሸጠችው /ለት/። ያም ዘይት ብፅዕት ማርያም እንተ ዕፍረት እስክትመጣ ድረስ ለብዙ ጊዜ በአርሱ ዘንድ በዚያ ኖረ።

፯ ያችም ማርያም እንተ ዕፍረት ከእሱ ገዝታ በጌታችን ሥጋ ላይ አፈሰሰችው። አስቀድመን እንደተናገርን።

፰ እነሆ ይህ ሽቱ ከጌታችን ዘንድ እንተገኘ አውቀን ተረዳን ያም በፈረስ ላይ ተቀምጦ ጌታችንን በጭኑ አቅፎ የያዘው ፈረሰኛ ሰው። ጌታችን በእንጨት መስቀል ተሰቀሎ ስለያመነበት ፈያታይ ዘየማን /ጥጦስ/ ነው።

፱ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ በጽኑ ሃይማኖት ታምኑ ዘንድ ይገባችኋል። የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርንም ድንቅ ሥራ አትመርምሩ አምናችሁ የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ ታገኛላችሁ።

፲ እግዚአብሔር በእናንተ ላይ ይባረክ /ይባርካችሁ/። ሥራችሁንም ያስምርላችሁ። ልጆቻችሁንም ይጠብቅላችሁ። ከክፉ ነገር ሁሉም ያድናችሁ። አምላክን አምላክን በወለደች በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት። በማርያም እንተ ዕፍረት ልመና፣ ለአብና ለወልድ ለመንፈስቅዱስም ምስጋና ይገባል። ዘላለሙ በእውነት ያለሐሰት ይሁን ይደረግ።

Scanned with CamScanner

፲፩ ወንጌልን በመጀመሪያ የጣፈ ወንጌላዊ ማቴዎስ እንደተናገረ ኢየሱስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የመላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ መደ እሱ ቀረበች። በማእድም ተቀምጦ ሳለ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ላይ አፈሰሰችው።

፲፪ ደቀመዛሙርቱም ይህን አይተው ተቆጡና ይህ ጥፋት ለምንድን ነው? ይህ በብዙ ዋጋ ተሸጦ ለድሆች ምጽዋት ሆኖ በየጊዜውና በየስዓቱ ስናገኛቸው ሊሰጥ ይችል ነበርና አሉ።

፲፫ ኢየሱስ ጌታም ይህን አውቆባቸው እንዲህ አላቸው መልካም ሥራ በእኔ ላይ አድርጋለችና። ይችን ብፅዕት ማርያም እንተዕፍረትን ለለምን ታደክሙአታላችሁ?። ድሆች ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና በወደዳችሁት ጊዜ ታደርጉላቸዋላችሁ እኔ ግን ዘወትር የምታገኙኝ አይደለሁም። እርስዋ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች /የመቃብሬን ቀን አስጠብቃዋለች/።

፲፬ እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህን ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ሰፈር በምትሰብኩበት ይች ማርያም እንተ ዕፍረት ያደረገችው ለእርስዋ መታሰቢያ እንዲሆናት ይናገራል። ማቴ፳፮፡፮-፲፫ ለዘለዓለሙ አሜን።

ምዕራፍ ፲፩ የቀዳሚት

፩ ዳግመኛም ጌታችን በማርቆስ ወንጌል እንዲህ አለ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት በነበረ ግዜ በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፡ ያን ጊዜ የተመረጠች ማርያም እንተ ዕፍረት ዋጋው እጅግ የከበረ ጥሩ ናርዶስ ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልጣቅ ይዛ መጣችና ብልጣቁንም ከፍታ በእራሱ ላይ አፈሰሰች።

Scanned with CamScanner

፪ አንዳንዶችም ይህ የሽቱ ጥፋት ለምንድርነው? ይህ ሽቱ ከሦስት መቶ ዲናር በሚበልጥ ዋጋ ተሸጠ ለድሆችና ለጦም አዳሪዎች ሊሰጥ ይቻል ነበርና ባልተቻለም ነበርን ብለው በራሳቸው ይቆጡ ነበር እርስዋንም ነቀፏት።

፫ ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ ይችን ብፅዕት ማርያም እንተ ዕፍረትን ተዋት ለምን ታደክሙአታላችሁ መልካም ሥራ ሠርታለች አላቸው።

፬ ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና በማንኛቸውም በወደዳችሁት ጊዜ መልካም ልታደርጉላቸው ትችላላችሁ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም። እርስዋም የተቻላትን አደረገች። አስቀድማ ለመቃብሬ ሥጋዬን ቀባችው።

፭ እውነት እላችኋለሁ ይህ ወንጌል በዓለሙ ሁሉ በማንኛቸውም በሚሰበክበት ሥፍራ እርስዋ ያደረገችው ለእርስዋ መታሰቢያ ሊሆን ይነገራል። ማር፲፬፡፫-፱ የክርስቲያን ወገን ሁሉ ከፍ ከፍ ያደርግዋታል። ለዘአዓለሙ በእውነት።

፮ ወንጌላዊ ሉቃስም እንደተናገረ ከፈሪሳውያንም አንዱ ከእርሱ ጋር ይበላ ዘንድ ለመነው። በፈሪሳዊው ቤትም ገብቶ በማዕድ ተቀመጠ።

፯ እነሆም በዚያች ከተማ ከሚኖሩ ሰዎች ተለይታ ሐጢአተኛ የነበረች የተመረጠች ብፅዕት ማርያም እንተ ዕፍረት በፈሪሳዊ ቤት በማዕድ እንደተቀመጠ ባወቀች ጊዜ የአልባስጥሮስ ሽቶ አመጣች።

፰ በስተኋላው በእግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች በእንባዋ እግሩን ታርስ ጀመረች። በራስ ጠጕርዋም ታብሰው እግሩንም ትስመው ሽቱም ትቀባው ነበር።

Scanned with CamScanner

፱ የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ ይህስ ነቢይ ቢሆን ይች የምትዳሥሠው ሴት ማን እንደሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ አሰበ።

፲ ጌታም መልሶ ስምዖን ሆይ የምነግርህ ነገር አለኝ አለው። እሱም መምህር በል ተናገር አለ።

፲፩ ለአንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት በአንዱ አምስት መቶ ዲናር ነበረበት በሁለተኛውም ሃምሳ ነበረበት። የሚከፍሉትም ቢያጡ ለሁለቱም ተወላቸው። እንግዲህ ከእነሱ አብልጦ የሚወደው ማን ነው?።

፲፪ ስምዖንም መልሶ ተናገር ካልኽስ ብዙ የተወለት ይመስለኛል አለው። እሱም በእውነት ፈረድህ አለው።

፲፫ ወደ ሴቲቱም ዘወር ብሎ ስምዖንን እንዲህ አለው ይችን ሴት ታያትአለህ? እኔ ወደቤትህ ገባሁ ውኃ እንኪን ለእግሬ አላቀረብህልኝም ብዕዕት ማርያም እንተ ዕፍረት ግን በእንባዋ እግሬን አራሰች የሐር ጉንጉን በመሰለ ጠጉርዋም አበሰች።

፲፬ አንተ አልሳምኽኝም እርስዋ ግን ከገባሁ ጀምሮ እግሬን ከመሳም አላቋረጠችም። አንተ ራሴን ዘይት እንኪን አልቀባኽኝም እርስዋ ግን እግሬን ሽቱ ቀባችኝ።

፲፭ ስለዚህ እልሃለሁ እጅግ ወዳኖለችና ብዙ ያለው ኃጢአቷ ተሠርዮላታል። ጥቂት የሚሠረይለት ጥቂት ይወደኛል ብዬ እነግርህአለሁ።

፲፮ እርስዋንም ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል አይዞሽ አላት።

Scanned with CamScanner

፲፯ ከእርሱ ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩት በልባቸው እንዲህ አሉ።
ኃጢአትን እንኪን የሚያስተሠርይ ይህ ማን ነው ይሉ ጀመር።

፲፰ ብፅዕት ማርያም እንተ ዕፍረትንም ሃይማኖትሽ አድኖሻል በሰላም ወደ
ቤትሽ ሂጅ አላት። ለዘዓለሙ በእውነት ያለ ሐሰት።ሉቃ፯፡፶፭-፯

፲፱ ወንጌላዊ ዮሐንስ እንደተናገረ። ከፋሲካ በፊት በስድስተኛው ቀን
ኢየሱስ ከሙታን ለይቶ ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ
ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ መጣ።

፳ በዚያም እራት አደረጉለት ማርታም ታገለግል ነበር። አልዓዛር ከእርሱ
ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበር።

፳፩ ማርያምም እጅግ ዋጋው የበዛ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወሰዳ
የጌታ ኢየሱስን እግር ቀባች በጠጉርዋም እግሩን አበሰች፡ ቤቱንም
የናርዶስ ሽቱ መላው።

፳፪ ነገር ግን ከደቀመዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ
የአስቆሮቱ ይሁዳ ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች
ያልተሰጠ ስለምንድን ነው? አለ።

፳፫ ይህንም የተናገረ ሌባ ስለነበር ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው
አይደለም። ከረጢትም ይዞ በውስጡ የተሰበሰበውን ከመባው ገቢ
ይወስድ ስለ ነበር ነው።

፳፬ ጌታ ኢየሱስም ለምቀበርበት ቀን እንድታስጠብቀው ተዋት አለው። ድሆች
ግን ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና በወደዳችሁት ቀን.
ታደርጉላቸውአላችሁ። እኔ ግን ዘወትር ከእናንተ ጋር አልኖርምና ሁል
ጊዜ የምታገኙኝ አይደለም አለ። ዮሐ. ፲፪፡ ፭-፱ ወንጌል በተሰበከበት
ሁሉ ያስቧት ብሎ በቃሉና በቅዱስ ወንጌል እንዳመሰገናት።

Scanned with CamScanner

፳፪ በአሁድ ቀን የሚነበብ የማርያም እንተ ዕፍረት ገድል

ምዕራፍ ፲፪።

፩ እኛም ሕዝበ ክርስቲያን ሁላችን የብፅዕት ማርያም እንተዕፍረትን በዓሏን እናከብር መታሰቢያዋን እናድርግ ለነፍሳችን ድኅነት ይሆን ዘንድ ጻድቁን በጻድቁ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይቀበላል ያለ ጌታችን በማይታበል ቃሉ ቃል ኪዳን እንደገባላት መጠን።

፪ እንደዚሁ ሁሉ ከዚች ከቅድስት ማርያም እንተዕፍረት በረከቷንና የረድኤትዋን ስጦታ ገንዘብ እናድርግ።

፫ እናመሰግናት ስሟን እናክብር መታሰቢያዋንም እናደርግ ዘንድ ስለ እርስዋ ፍቅር የተሰበሰብን ሁላችን ኑ እናመሰግን።

፬ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለኛ ሲያስተምር እንደተናገረ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል፣ መከራ፣ ውይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ዕራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ብሎ እንደተናገረ።

፭ ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎችም ሆን ብሎ መጽሐፉ እንደተናገረ። ሮሜ. ፰:፴፮ መዝ ፵፭

፮ ሠይጣንን ስለእኔ ድል ነሥተው እኔን እንዚህ አድርገው የሚወዱኝን እኔ በሰማያዊ አባቴ ፊት እንዲህ እላቸዋለሁ። ዓለም ከመፈጠሩ ጀምሮ ወደ አዘጋጀሁላችሁ ወደ አገሬ መንግሥተ ሰማያት ኑ እላቸዋለሁ። ዓይን ያላየው ጆሮ ያልሰማው፣ በሰው ልቡና ያልታሰበ አባቴ በመፍረጃው ቦታ ለወዳጆቹ የዘጋጀው።

፯ አሁንም ወዳጄ ማርያም እንተዕፍረት ሆይ በእኔ ደስ ይበልሽ የምሰጥሽን ለምኚኝ። የልብሽን ልመናም እሰማለሁ የአሰብሽውንም እጨመርልሻለሁ።

Scanned with CamScanner

፰ ስምሽንም የሚጠራውን የክርስቲያን ወገን ሁሉ በአማያልፍ ዘላለዓለማዊ መንግሥቴ ሥርየትን አሰጠዋለሁ::

፱ አቤያተክርስቲያናትን እየሳበኝ መታሰቢያሽን የሚያደርገውን ሁሉ እንደሚገባ እንግዳ እየተቀበለ ተጨንቆ ተቸግሮ የሚሰጥም ቢሆን ለድሀውና ለምስኪኑ የሚራራ ቢሆን፣ በንግሥሽ ቀን ይቅርታ የሚያደርገውም ቢሆን አዝኖ እንደሚገባ መታሰበሽን የሚያደርገውን፣ ዕጣኑን፣ ወይኑን፣ መስዋዕቱን፣ መብራቱን፣ ጧፉን እንደሚቻለው መጠን የሚያስገባውን ይቅር አለዋለሁ:: በልዕልና ባለች በኢየሩሳሌም ለዘለዓለም ጸንተው ይኖራሉ የኃጢአትንም ሥርየት አሰጣቸዋለሁ::

፲ በስምሽ ቤተክርስቲያን የሚሠራውን ቢሆን ሚጠራቸውን የአንቺ እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ ከሆኑ ገድልሽን ድንቅ ስራምችሽን የሚፅፈውን:: ወይም በፍቅርሽ ሽቶ የተግፈውን የሚያነበውንና ቢሆን በብረታት የተባሰውን የሚሰማውን እሊህን ሁሉ እኔ እራሴ ወደ እኔ ዘንድ እቀበላቸዋለሁ አስገባቸዋለሁ ከአፌ የወጣ ቃሌን አሱ አልልም::

፲፩ ለወዳጄ ለማርያም እንተዕፍረት በእራሴ ማልሁ መሐላዬም አይዋሽም:: ለዘለዓለሙ ከእኔ ጋር ጸንቶ ይኖራል:: በእውነት ያለሐሰት::

፲፪ እግዚአብሔር የማርያም እንተዕፍረትን ወዳጆች ይማራቸው:: መንግሥተ ሰማያትንም ያውርሳቸው:: ይቅር ይበላቸው ኃጢአታቸውንም ያሥተሰርይላቸው:: ያነበበውን፣ የተረጎመውን፣ የተነበበውን ቃላት የሰማውንና ሰምቶም የተቀበለውን እሊህን ሁሉ በአንድነት በመንግሥተ ሰማያት ይማራቸው:: ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል:: ይቅርታውና ቸርነቱ እስከዘለዓለሙ በእኛ ላይ ይሁን በእውነት ያለ ሐሰት ይሁን ይሁን::

Scanned with CamScanner

አንደኛ ተአምር

ልመናዋ ክብሯ ከአገልጋይዋ ከተስፋ ሚካኤል ጋር ይሁንና ይች ንዕድ ክብርት ማርያም እንተዕፍረት ያደረገቸው ተአምር ይህ ነው። ለዘለዓለሙ በእውነት ያለሐሰት ወንድሞቼ ይች የተመረጠችና ክብርት የምትሆን ማርያም እንተዕፍረት በሸዋ አውራጃ በአንዲት አገር ያደረገችውን ተአምር ስሙ። በዚያች አገር ንዕድ ክብርት ምትሆን ማርያም እንተዕፍረትን የሚወድ አንድ መነኩሴ ነበር። የዚያችን አገር ሰምች እንደዚህ አላቸው ንዕድ ክብርት የምትሆን ምርጥ ዕቃ ማርያም እንተዕፍረትን በዓል ኑ እናክብር አላቸው። እነሱ ግን አይሆንም ብለው በሰንሰለት አሰሩት። እንደዚህም አሉት አስቀድመን የማናውቀው በዓል ያመጣህብን ምንድን ነው? ብለው በዚህ መለረት አጽንተው ተጣሉት እሱ ግን ወደ አገር ገዢው ላክ አገር ገዢውም የመነኩሴውን መልእክት ፈጥኖ ሰማው ወደ እነሱም እንደዚህ ብሎ ላክ ያን መነኩሴ ፍቱት ያችን ማርያም እተዕፍረትንም አክብሯት ከፍከፍም አድርጓት ብሉ። ከዚህ በኋላ እነዚያ ሰምች ያንን መነኩሴ ፈቱት ማርያም እንተዕፍረትንም በገዢው ቃል ከዚያ ቀን ጀምሮ አከበሯት ከፍከፍም አደረጓት ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከፍከፍ አለች። ልመናዋ በረከቷ ከወዳጅዋ ከተስፋ ሚካኤል ጋር እንዲሁም ከመላው ክርስቲያን ጋር ይሁን ለዘለዓለም ዓለም አሜን።

Scanned with CamScanner

ሁለተኛ ተአምር

ልመናዋ ክብሯ ከአገልጋይዋ ከተሰፋ ሚካኤል ጋር ይሁንና ይች ንዕድ ክብርት ማርያም እንተዕፍረት ያደረገቸው ተአምር ይህ ነው። ለዘለዓለሙ አሜን። ቅድስትና ብፅዕት የምትሆን ይችን ማርያም እንተዕፍረት የምትወዷትና የምታከብርዋት የቤክርስተያን ልጆች አባቶቼ እና ወንድሞቼ ሆይ ለወዳጇ ለአንድ ዲያቆን ያደረገችለትን ስሙ በአንዲት አገር አንድልጅ ነበር። ያም ልጅ ከእለታት አንድ ቀን የዲቁና ሹመት ለመቀበል ገብርኤል ወደሚባል ጳጳስ ይሄድ ዘንድ ተነሣ። ከጓደኞቹ ከአምስቱ ዲያቆናት ጋር የዲቁናውን ማዕረግ ተቀብሎ ሲመለስ ያ ልጅ ጥኑ በሽታን ታመመ። መንገዱንም በእግሩ መሄድ ተሳነው። ወንድሞቹ /ጓደኞቹ/ ዲያቆናት እንዲህ አሉት። ወደ አገራችን እንደርስ ዘንድ እኛ ትተንህ ልንሄድ ነውና ሥንቃችንን ከፍለህ ስጠን አንተ ግን ፈጽመህ ታመሃል ስለዚህ ከአንተ ጋር መቆየት አንችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር ይርዳህ። እነዚህም ዲያቆኖች እንደዚህ ብለው ይህን ከተናጉ በኋላ በጤንነታቸው እየታጀሩ ያን ዲያቆን ትተውት ሄዱ። ያም ልጅ ከመንገድ ዳር ከዋርካ ዛፍ በታች /ሥር/ ተኝቶ በጎዳና መካከል እያለቀሰ ከአንድ ዲያቆን ጋር ቀረ። ወደ አያቱ ዛር እንዲህ እያለ ይለምን ጀመር አንተ የአያቴ ዛር ሆይ ከዚህ ፅኑ በሽታ ያዳንከኝ እንደሆነ ለአንተ የሚጎዘጎዝ ሣር አጭድልህአለሁ። በዚህ በአያቱ ዛር ከተማፀነ በኋላ ይችውም አባቱ እናትናት። የሚረዳው ከደዌውና ከጽኑ በሽታው የሚያድነው አለገኘም። ዳግመኛ ፈጽሞ አለቀሰ አበቶቼን የረዳሻቸው ቅድስት ማርያም እንተዕፍረት ሆይ እንደዚህ እኔንም ከዚህ በሽታ ፈውሺኝ እያለ ብዐዓት ገባ

Scanned with CamScanner

እነደዚሁ እኔንም ከዚህ ከያዘኝ ጽኑዕ በሽታ አድኂኝ እያለ ብፅዓት ገባ። ይህን ተናግሮ እንባውን ወደ ሰማይ ረጨ። የዚያን ጊዜ ከበሽታው ድኖ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ቅድስትና ብፅዕት የምትሆን የማርያም እንተ ዕፍረትም ድንቅ ሥራ እያደነቀ መንገዱን ሄደ ቅድስትና ንዕድ ክብርት የምትሆን የማርያም እንተዕፍረት ልመናዋ በረከቷ ከወዳጅዋ ከተስፋ ሚካኤል ጋር እንዲሁም ከመላው ክርስቲያን ጋር ይሁን ለዘለዓለም ዓለም አሜን።

Scanned with CamScanner

ለላም ለእስትንፋስኪ መዓዛዚአሁ ዘሠነየ። ወለገ·ርዔኪ ሰላም ሐሊበ መንፈስ ዘሰትየ። እንተዕፍረት ክብርኪ አምክብረ ቅዱሳን ዘዐብየ። እሴሮ በኪዳንኪ ከመኢይበል ወይልየ። እስመዘእንበኪ ረዳኢ አልብየ።

ለላም ለከሣድኪ ዘዐነቀ ወርቀ ·ነለቀት ዘበአማን። ለመ·ተክፍትኪ ሰላም ወለዘባንኪ ገርዜን። እንተዕፍረት ስብሕት ዘአፍቀረኪ መድ·ን። እቀብኒ እግዚእትየ እምዘመነ ዕልወት ሳምን። ከመየአቅቦ ለብንት ቀራንብት ዘዓይን።

ሰላም ለእንግድዓኪ ዘኢይትነገር ኵነቱ። ለሕፅንኪ ሰላም ወለአደው·ኪ ክልኤቱ። እንተዕፍረት ንግሥት ለእግዚአብሔር መርዓቱ። ሠውርኒ እግዝእትየ እመደንግጸን ሠለስቱ። እስመኪዳንኪ ኮነ በቋዔ ባሕቲቱ።

ሰላም ለመዛርዕኪ ወለኵ·ርናዕኪ ዘኃይል። ለእመታትኪ ሰላም ወለእረኃኪ ወንጌል። እንተ ዕፍረት ጸሐፌ በብርዐ አእምሮ ልዑል። እመረቀ ልብየ በልቡ·ናኪ ፊደል። ከመያንብብዋ ድልዋን ለሣህል።

ሰላም ለአፃብዕኪ እግረ አምላኩ ዘሐፀበ። ለአጽፋ·ረዕዴኪ ስላም ወለገቦኪ ሰከበ። እንተዕፍረት የዋሒት ዘተመሰልኪ ርግበ። አጥብው·ኒ እግዝእትየ እምሐሊበዘአኪ ጥበ። ከመ እኩ·ን አነ ወልድኪ ጠቢበ።

ሰላም ለከርሥኪ ወለልብኪ ማዕነቅ። ለኵ·ልያትኪ ሰላም ወለሕሊናኪዕሙቅ። እንተ ዕፍረት ምዕዝት ዘገነተ ሰማይ አርዘአጽቅ። አው·ፅእኒ እግዝእትየ እምተኃላሎ ወድድቅ። በከመአው·ፅኦ ቀዲሚ ለነቢይ ፃድቅ።

ሰላም ለአማዕ·ትኪ ፊለገ ር·ነራኄ ዘኮነ። ወለንዋየው·ስጥኪ ሰላም ዘመጠላፅተ ከርሥ ተከድነ። እንተ ዕፍረት ምዕዝት አምላለ ደናግል ዕጣነ። በው·ዐ·ይ አንብዐ ገጽ ከመሐፀብኪ መድ·ንኒን በማየ ንስሓ ኪያየ ሕፅቢፍጠ·ነ።

ዘጸውዐ ሰመዪለኪ ለሰጊዜ ጸባሕ ወነግህ። ጎጡአተስፋ ገብርኪ እምፃታ ታዘንብዙጎ። እንተዕፍረት ወይን ፀዋራተ አሰካል ንፁሕ። ያጽምፅ ዕዝነልብኪ ወኪደንኪ ርጎሩጎ። ዘከመ አጽምዐ ስዕለቶ አመ አይጎ ለኖጎ። አምላከ ማርያም እንተዕፍረት እቀብኒ ወአድጎነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊቲ ለገብርኪ ተስፋ ሚካኤል። ለዓለመዓለም አሜን።

<u>በሰመልበ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብለን ያቋቋዘይት ጌቴሴማኒ እንተ ዕፍረት ማርያም ቤተክርስቲያንን ታሪክ መጻፍ እንጀምራለን።</u>

የቄላ ዘይት እንተ ዕፍረት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው ኢትዮጵያ በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን በግዳን ወረዳ 017 ቀበሌ በቄላ ዘይት ጌቴሴማኒ እንደ ግሸን ደብረ ከርቤ ዙሪያዋ በነጭ ገደል ተከቦ መስቀልኛ ሆኖ የመግቢያዋ በር አንድ ብቻ ሲሆን በውስጧ ግን የጥንድና የአስታ ዛፍ የበዛበት የዛፉ ብዛት ይህን ያህል ተብሎ በቁጥር የማይወሰን፣ በውስጧ አንበሶች እና ነብሮች የሚኖሩበት፣ ቅዱሳን ባሕታውያን ተሠውረው የሚፀልዩባት ሱባኤ ተገብቶት ከታሰበው ቀን ሳይደርስ በትንሽ ቀን የምትገለጥባት፣ ብዙ ታሪክ ሲታይባትና ሲነገርባት የኖረች አሁንም የሚታይባትና የሚነገርባት ታላቅና ታዋቂ ቦታ ናት። ይችውም ታሪካማ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት በ500 /ፎ፪/ ዓመተ ምህረት አንድ ግብፃዊ አባት ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የተነሣ ጽለቷን ከተለያዩ ብዙምች ጽላቶች ጋር ከግብጽ አምጥቶ የማርያም እንተዕፍረትን ጽላት ከዚህ ቄላ ዘይት ከተባለው ሀገር ልዩ ቦታም ጎረበስጌ ከምትባል ትንሽ ተራራ ላይ ትንሽ ጎጆ ሰርቶ ከዚያ ጽላቱን አስገብቶ በአከባቢው ያሉትን ሕዝበ ክርስቲያን ሰብስቦ ታቦት አምጭላችኋለሁ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ሰርታችሁ አስቀድሱ ብሎ አስረከባቸው።

ለጊዜው ፈጢኖስ ከሚባለው ሰው ቤት አሰገብተዋት ሄዱ::
እንደገና መምህር ዘሚካኤል የሚባሉ ሊቅ ብዙ ጊዜ ታቦቲቱ
ከዋሻ ውስጥ ተደብቃ ሰለኖረች ይችን ታቦት ለማስባረክ በአጼ
ፋሲል ዘመነ መንግሥት ጎንደር ሄደው ብዙ ጊዜ ደጅ ፀንተው
አስባርከው መጡ:: ከዚህ በኋላ ከዚሁ ተራራ ቤተክርስቲያን
ተሠርቶ እስከአሁን ድረስ ስትቀደስ ስትወደስ ትገኛለች::
ቦታዋም ግርምትና ድንቅዬ የባሕታውያን መገኛ የቅዱሳን
መነሀርያ፣ የጸሎት አውድማ፣ የረድኤት ጉልላት፣ የተአምራት
መገለጫ፣ የሱባዔ መግቢያ፣ ብዙ ተአመራት የተደረገባትና
የታየባት ቤተክርስቲያን ናት::

ቤተክርስቲያኗ ያደረገችው ተአምራት ብዙዎች ናቸው:: ከነዚህም
ለአብነት ያህል ጥቂቶቹ እንደ ሚቀጥለው ተዘርዝረዋል::

ፅኖ ይችን አገር እንደ ገል ቀጥቅጦ እንደ ሰም አቅልጦ ተሚገዛ
እንደ ፈርዖን ልቡ የደነደነ ራስ ቢሆነኝ የሚባል ጨካኝ ንጉሥ
ነበር:: ከክፋቱም የተነሳ በአራቱ መዓዘን የሚያሳይ ጥንግላ አምባ
የሚባል ትልቅ ተራራ አለ ከእሱ ቤቱን አሰርቶ ሲኖር ከእለታት
አንድ ቀን በዛሬው ቀን ቤት ሠርታችሁ ከድናችሁ፣ መርጋችሁ
አስረከቡኝ አላቸው:: ሕዝቡም ወንድም ሴትም ሳይቀር
ተሰብስበው ተካፍለን ቤት እንሥራ ተከፋለችሁ ደግሞ
ትከድናላችሁ የተረፈው ደግሞ ጭቃ ይርጉም ብለው ተማከሩ::
ከጭቃ ረጋሎቹ ብዙዎቹ ሴቶች ነበሩና እንዲት ሴት ነፍሰጡር
ነበረች ሰትረግጥ ምጥ መጣባት ንጉሥ ሆይ ምጥ መጣብኝ
እባክህ አሳርፈኝ አለችው:: እሱ ግን ክፉ ጨካኝ ንጉሥ ነውና

Scanned with CamScanner

ማርያም እንተ ዕፍረት ጠይም ሴት መስላ በጥፊ ስትመታኝ አየሁ ብሎ ሰውነቱ በትል ተከበ በመግል ተውጦ አይሆኑ ሆኖ በመንፈቁ /በ6 ወሩ/ ሞቷል።

፫ኛ አንድ ግለሰብኤ የማርያም እንተ ዕፍረትን እንጨት ቆርጦ ቤት ሰርቶ ተቀምጦ ሳለ ልጁን ድሮ ከቤተሰቡ ጋር ሲዘፍንና ሲያጨበጭብ እሳት ከወደ ሰማይ ወርዶ ንዋየ ቅድሳት ያለበትን ትቶ በቤተክርስቲያኗ እንጨት የተሠራውን ቤት አመድ አድርጎታል። አንድ ግለሰብኤም እንዲሁ የቤተክርስቲያኗን እንጨት ቆርጦ በድፍረት ቤቱን ሠራ። ቤቱ ተከድንኖ ሳያልቅ እንጨቱን በቆረጠበት መጥረቢያ አንገቱን ተቆርጦ ሞቷል። ልጁም ኢይሀድግ ወልድ ግብረ አቡሁ እንዲል የቤተክርስቲያኗን ጥድ ቆርጦ ሲሄድ ተያዘ። ቅፍቃፊ ነው እንጂ ደህና እንጨት አልነካሁም አለ። ወዲያው ቤት የሚያህል በሬ ነበረው ምንም ሳይነካው በቤተክርስቲያኑ እንጨት ድግፍ ብሎ ሞተበት። በዚህን ጊዜ ያ ሰው የቤተክርስቲያኑን እንጨት ቆርጬ በሀሰት ምዬ ነበር አሁን ግን ማርያም እንተ ዕፍረት መስከረችብኝ ብሎ ድንቅ ሥራዋን መስክሯል።

፬ኛ ማሪቤታ ካሣ ንጉሥ የሚባል አንድ ምሁር የንግሣ በዓል ደከመኝ ታከተኝ ሳይል ማርያም እንተ ዕፍረትን ያገለግል ነበር። ከእለታት አንድ ቀን የቅዱስ ሚካኤልን ቤተክርስቲያን ልሠራ ነው እባካችሁ ከቤተክርስቲያኑ ጥድ ስጡኝ ብሎ የደብሩን ሕዝብ

Scanned with CamScanner

ዕፍረትን አንቺን ያመነ በሰማይም በምድርም ከመከራ ይድናል ብሎ ድንቅ ሥራዋን መስክሯል።

፮ኛ ላዕከ ማርያም የሚባል ባሕታዊ የማርያም እንተ ዕፍረት ጽላት ካለበት ቤተክርስቲያን አድርሰኝ እያለ እግዚአብሔርን ሲለምን ይኖር ነበር። የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ እግዚአብሔር ማርያም እንተ ዕፍረት እንድትገለጽለት አደረገ። በተገለጠችለት ጊዜ አንቺ ሴት ማን ነሽ አላት። የማርያም እንተ ዕፍረት ጽላት ካለበት ቤተክርስቲያን አድርሰኝ እያልህ ስትጸልይ አልነበረምን? አለችው። አዎን እመቤቴ አላት።። እንኪያስ ማርያም እንተ ዕፍረት እኔ ነኝ ያለሁበት ቤተክርስቲያንም ዙሪያውን በነጭ ገደል የታጠረ ሆኖ መስቀለኛ ተቀምጦ በውስጡ በቁጥር የማይወሰን አፀድ ያለበት፡ አንበሶችና ነብሮች የሚኖሩበት፣ የቅዱሳን መናኸሪያ፣ የሱባዔ መጋለጫ፣ ድንቅዬና ብርቅዬ ቦታ ነው። ይህን ምልክት ይዘህ ሂድ አለችው። ከዚህ በኋላ ባሕታዊ ላዕከ ማርያም እየጠቀየ ማርያም እንተ ዕፈረት ሳትለየው ከዚች ታላቅ ቦታ ደረሰ። በዚች ቦታ በተራቀን አራዊትና የበቁ ቅዱሳን እንጂ ሰው አይገኝምና ቤተክርስቲያኑን ተሳልሞ ጸሎቱን ጸልዮ ከጨረሰ በኋላ ከጥድ ስር አረፍ ብሎ ሲያዳምጥ አንድ አንበሳ መጣ። ጥቂት እንደተቀመጠ (ቆጭ እንዳለ) ከተሠወሩት መናንያን አንድ መናኝ መጥቶ ወንድሜ ደህና ውለሃል አለው። እሱም ድንግጥ ብሎ ዝውር ቢል

Scanned with CamScanner

አሱም መልከ መልካም ነበርና መልከ ማማር ኃጢአት ከሆነማ ብሎ ፈጣሪዬ ሆይ በመልኬ ማማር ኃጢአት እንዳልሠራ ሰውነቴን በቀኖል እና በመግል ዋጠው በትል ከበበው እያለ እንደ ገብረ መርዓዊ ቢጸልይ እጹና እግሩ ተቆርጦ መግል እየዘነበበት ትላትል እየፈሉበት ሲኖር ማርያም እንተ ዕፍረት እየመጣች አንበሶችንና ቅዱሳኖችን የጢሙንና የራሱን ፀጉር እንዲላጩትና ጥፍሩን እንዲቆርጡት ታዝዘለች ነበር። እነሱም የማርያም እንተ ዕፍረትን ትዕዛዝ ሰምተው ፀጕሩን ይላጩት ጥፍሩን ይቆርጡት ነበር። ከዚህ በኋላ በዚች ቦታ እንደ አብርሃም እንግዳ የሚቀበል አቶ ሰማው ደሴ የሚባል አንድ ደግ ሰው ነበር።

በተለይ የመነኮሳትን እንግዳ የሚያርፈው ከእርሱ ቤት ነው። እየሄደ ባሕታዊ ላዕከ ማርያምን ይጠየቅ ነበር። አባ ላዕከ ማርያም በቅቶ ስለነበር እንደ ቅዱስ ድሜጥሮስ አንተ ኃጢአተኛ ነህ ሥጋ ወደሙ አትቀበል አንተ ግን በቅተሀልና ተቀበል እያለ ያግድ /ይከለክል ነበር/። እንደዚሁም ይህን ሰውዬ አንተ አሁን አርባ አመት ሆኖህል ስለዚህ ሥጋ ወደሙ ተቀበል በኔ አጽዋማት በበዓላት ከሴት እንዳትደርስ ብሎ የቤተክርስቲያኑን ሥርዓት አስተምሮ ባርኮ ሰደደው። አቶ ሰማው ደሴ ከዚያ ቀን ጀምሮ የባሕታዊ ላዕከ ማርያምን ትምህርት ቀስሞ ሥጋ አምላክን ተቀብሎ አጽዋማትን እየጸመ በዓላትን እያከበረ

ነገራቸው። ከዚህ በኋላ ካህናቱም ሕገዘቡ ይቅር ተባብለው አንድ ሆነው ደስ ብሏቸውም ወደ መቅደሱ ታቦታቸውን አስገብተዋል።

፮ኛ አገራቸው የማይታወቅ ሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች ከዚች ታሪካማ ቤተክርስቲያን ሱባዔ ገብተው ከጸለዩባት ማርያም እንተ ዕፍረት ተገልጣ ታነጋግራለች ሲባል በወሬ ሰምተው ሊጸልዩ ቢገቡ ሰዎች አገኟቸው። አይተውም ምንድን ናችሁ ብለው ጠየቋቸው። እነሱም ተማሪዎችን ከዚህ ቦታ የጥድ ዛፍ ስላለ መምህሮቻችን የጥድ ፍሬ ለቅማችሁ ኑ ብለውን ነው ብለው አመካኝተው ፍሬ ይለቅሙ ጀመሩ። ሰዎቹ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ከበረሃ ውስጥ አንበሳ አገኛቸው እሱም እየመራ ወስዶ ከሱባዔ ቦታ አደረሳቸው። በዚህ ዕፁብ ዕፁብ እያሉ ሲደነቁ ከተሠወሩት ቅዱሳን አንዱ ወጥቶ በርቱ እንጅ አትፍሩ እንዳትጮሁ ሆናችሁ ጸልዩ ማርያም እንተ ዕፍረት ትገለጥላችሁአለች ብሏቸው ተሠወረ። እነሱም ሲጸልዩ ቅድስት ማርያም እንተ ዕፍረት ተገልጣ አነጋገረቻቸው። እየተደሰቱ ከቤተክርስቲያኑ በርሃ ሲወጡ እንደ መጀመሪያው አሁንም ሰዎች አገኟቸው። ይች ቤተክርስቲያን ታሪካዊ ናት ሱባዔ ገብተን ነበር ተገልጣ አነጋገረችን እያሉ አድንቀውላቸዋል።

፯ኛ አንዲት ሴት ትዳር መስርታ ልጆች ወልዳ ስትኖር ሠይጣን አዕምሮዋን ነስቷት በረሃ ለበረሃ እያደረች ስትዞር ከዚች ተአምረኛ ቤተክርስቲያን ደረሰች። ስትላለም አእምሮዋ

የጌታችን ፩፻፳ /120/ ቤተሰቦች ስም ዝርዝር ፲፪/12/ ሐዋርያት፣ ፸፪/72/ አድርእት፣ ፴፮/36/ ቅዱሳን አንስት ናቸው።

፲፪/12/ ሐዋርያት

፩ ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስ
፪ ዮሐንስ ወልደ ዘብዲዮስ
፫ እንድርያስ የጴጥሮስ ወንድም
፬ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ
፭ ፊልጶስ ነገደ ዛብሎን
፮ በርተሎሜዎስ
፯ ማቴዎስ ሌዋዊ
፰ ቶማስ ዘሕንደኬ
፱ ያዕቆብ ወልደ አልፍዮስ
፲ ታዴዎስ ዘነገደ ዮሴፍ
፲፩ ናትናኤል ዘቃና ዘገሊላ
፲፪ ማትያስ ተክለ ይሁዳ

፸፪/72/ አድርእት፣

፩ ማርቆስ ሊቀ አርድእት
፪ ሉቃስ ወንጌላዊ
፫ አስጢፋኖስ ሊቀ ዲያቆናት
፬ ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ
፭ ጢሞቴዎስ
፮ ሲላስ
፯ በርናባስ
፰ ቲቶ
፱ ፊልሞና
፲ ቀሌምንጦስ
፲፩ አልአዛር ከመቃብር የተነሣ
፲፪ ስምዖን ዘለምጽ
፲፫ ዘኬዎስ ከሾላ ዛፍ የወጣው
፲፬ ቆርኔሌዎስ መቶ አለቃው
፲፭ አጋቦስ
፲፮ ጤርጥዮስ /ጢባርዮስ/
፲፯ አግነጢዮስ ሕፃን
፲፰ አብሮኮሮስ የዮሐንስ ረድእ
፲፱ ማልኮስ
፳ አንሲፎሮስ
፳፩ ኤርስጦስ
፳፪ ጋይዮስ

Scanned with CamScanner

ፀቮ ኢያሶን
ፀፀ ጴውሎስ
ፀፁ ዲዮናስዮስ
ፀፂ ፊልጶስ
ፀፃ አናስሞስ
ፀፄ ጠራሚና
ፀፅ ጢሞና
ፀፆ ዮሴፍ
ፀ ኒቆላም
ፀፈ ይሁዳ
ፀፉ ያዕቆብ
ፁቮ ኒቆዲሞስ
ፁፀ አፍሮዲጡ
ፁፁ ሰልዋኖስ
ፁፂ ገማልያል
ፁፃ እንድራኒቆስ
ፁፄ ጵርስቅላ
ፁፅ ሐናንያ
ፁ ቴምፍሎስ
ፁፈ አቂላ

ፃፀ ጲላጦስ
ፃፁ ዩልያን
ፃፂ ዩልያን
ፃፃ ኤርባኖን
ፃፄ ኤጤሌን
ፃፅ ስንጣክን
ፃፆ ሄሮድዮና
ፃፈ ጢሮፊሞስ
ፃፉ ሉቅዮስ
ፃ አስክሮጦስ
ፃፊ ሱሲ ጴጥሮስ
ፄቮ ጵሮኮሮስ
ፄፀ እራስጥሮክስ
ፄፁ ኒቀሮናን
ፄፂ ኤጳፍራስ
ፄፃ ኤዮስጦስ
ፄፄ አስተራትዮስ
ፄፅ አኪላስ
ፄፆ ቲቂኮስ

ፅቮ ፕፕሮፊሞስ
ፅፀ ክረስቶፎሮስ
ፅፁ ዩልያል
ፅፂ ኤሊሞን
ፅፃ አርንያናስ
ፅፄ አርክበንዮስ
ፅፅ ምረናስ
ፅፆ አለአስክንድሮስ
ፅፈ ኤጴንጤስ
ፅፉ አስክሮስ
ፆቮ ሳልሞን
ፆፀ ሳፎን

፩ ሰሎሜ

፪ የዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ

፫ ማርታ የአልዓዛር እህት

፬ ማርያም እንተ ዕፍረት

፭ ማርያ

፮ ማርያም መግደላዊት

፯ ማርያም የዮሴፍ ሚስት

፰ ማርያም የቀለዮጳ ሚስት

፱ ዮሐና የኩዛ ሚስት

፲ ሐና ነቢይት

፲፩ ልድያ

፲፪ ሶስና

፲፫ ጣቢታ

፲፬ ፌቬን

፲፭ ጣርሲዳ

፲፮ ከርፍሌንያ

፲፯ ሮዴ

፲፰ በርስዓ የዮናስ እናት

፲፱ ሶፍያ

፳ ዮስቴና

፳፩ ከነናዊት

፳፪ ጲስ

፳፫ አላጲስ

፳፬ አጋጲስ

፳፭ ቅድስት አርሴማ

፳፮ ዕንባ መሪና

፳፯ አርኒ

፳፰ እሌኒ

፳፱ ኢየሉጣ

፴ ቴክለ

፴፩ ማርያም ግብጻዊት

፴፪ አትናስያ

፴፫ ሚልቴዲ

፴፬ ቤርዜላ

፴፭ ሚልቴዳ

፴፮ ቤልዜሊ

Scanned with CamScanner

፩. ማርያም ድንግል
፪. ማርያም መግደላዊት
፫. ማርያም የፋታይ ዘየማን እሕት
፬. ማርያም የመሰሌ እሕት
፭. ማርያም እንተ ዕፍረት
፮. ማርያም ግብጻዊት
፯. ማርያም የዮዶር ልጅ
፰. ማርያም የቀለዮጳ ሚስት
፱. ማርያም የቆላ እናት
፲. ማርያም የእመቤታችን እሕት
፲፩. ማርያም የሐና እሕት
፲፪. ማርያም የአንዮስ እናት

ዐሥሩ መዓርጋት

፩ የንጽሐ ሥጋ መዓርጋት

ሀ. ጽማዌ የዚህ ዓለምንሥራ ይነቃሉ
ለ. ልባዊ ቅዱሳን ንጹሐን ናቸው
ሐ. ጣዕመ ገማሬ

፪ የንጽሐ ነፍስ መዓረጋት

ሀ. አንብዕ አንብዐ ንስሐ
ለ. ኩነኔ ሥጋቸው ለነፍሳቸው ይገዛሉ
ሐ. ፍቅር ሁሉን የመውደድ ሀብት ነው
መ. ሐሠት በደመና ይጓዛሉ

፫ የንጽሐ ልቡና መዓርጋት

ሀ. ንጸሬ መላእክት
ለ. ተሰጥሞ ውስተ ባሕረእሳት
ሐ. ከዊነ እሳት/ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ/ በብርሃን ይከበባሉ።

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈፀመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን።

Scanned with CamScanner



መ/ር ተስፋሚካኤል ፈለቀ
የትርጓሜ መጽሐፍትና የቅኔ መምህር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሀይማኖት ጸንታችሁ የአጋንንትንና የመናፈቃንን ውጊያ ታግሳችሁ ሀብተውልድና ስመ ክርስትና የተቀበላችሁ በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኛችሁ የልዑል እግዚአብሔር ቤተሰቦች የቅድስት ድንግል ማርያም የእሸራትና የበኩረት ልጆች በመላእክት፤በነቢያት፤ በሐዋርያት፤ በቅዱሳን፤ በሰማዕታት አማላጅነት የምታመልኩ አባቶች፤ ወንድሞች፤ እናቶችና እህቶች የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ ቅድስት ማርያም እንተ ዕፍረት በሰው ላይ ሞት መኖሩን አስባ በገነዘቢ ሽቶ ገዝታ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሆና በንሰሐ የወረሰቻትን መንግሥተ ሰማያት እንወርስ ዘንድ ንሰሐ ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንሰሐ ግቡ ማቴ ፫፤፩ ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ ሆሴዕ ፮፤፩ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበዙ ማቴ ፬፤፯ ለጠያቂዎችን ወደ ንሰሀ ልጠራ ነው እንጂ ጻድቃንን ልጠራ